ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the Source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3፣ ሚያዚያ 2007

## የማህበረሰብ ዕድገት በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

“ይህን ትልቅ መስዋእትነት እየከፈለ ያለው የአካባቢው ሕብረተሰብ ነው፡፡” ... 9

ዶ/ር ዋሴ አንተነህ

ጊዜ እና ጊዜአችን ... 11

ነብዩ ንጉሴ

ያልተከደነው ትዳር

አጭር ልብወለድ

ፍሬዘር ታሪኩ

የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ ... 6

ፈታሒ በቃሉ




African Universities Presidents and Vice-chancellors made debate on “Secularism and Politicized Faith in Africa” at Bahir Dar University



BDU and Al Zaeim Al Azhari University signing memorandum of understanding

የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት ለሴት ተማሪዎች የማማከር ስልጠና ሰጠ ... ገጽ 4

ተቋሙ አለም አቀፍ ጉባዔ አካሄደ... ገጽ 5

የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዝዳንቶች ክርክር አካሄዱ... ገጽ 5

እውነትን መፈለግና ለሲሳው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

**Core Values**

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility

# ናይል ጋዜጣ

**በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**
**የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል**
**የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ**

**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጆች**
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ
አብነት ሰለሞን

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
የኑስ ኑሬ
ነብዩ ንጉሴ
ፍሬዘር ታሪኩ

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው

ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

# መልዕክቶችና አስተያየቶች

## ርዕሰ-አንቀጽ

### ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መቻቻልን ተግባራዊ በማድረግ ችግር ፈቺ መሆን ይጠበቅባቸዋል!

በዚህ በያዝነው ወር በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ቻንስለሮች ከሃይማኖትና ከፖለቲካ ነጻ የሆነ አስተሳሰብ በማፍለቅና ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት በመፍጠር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሚና ላይ ክርክር ማካሄዳቸው ይታወሳል፡፡ ፕሬዘዳንቶቹ በክርክራቸው ወቅት የአልሻባብ ታጣቂዎች በኬንያ ጋሪሳ ዩኒቨርሲቲ ንፁሃን ተማሪዎች ላይ ያደረሰውን ጥቃት እንዲሁም በሠሜናዊ ናይጀሪያ የቦኮ ሀራም አሸባሪ ቡድን በ300 ልጃገረዶችን ላይ ያደረገውን የእገታ ድርጊት በጽኑ አውግዘዋል፡፡

ሽብርተኝነት በአህጉሪቱ ላይ እያስከተለ ያለው ችግር ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ በቅርቡም በሊቢያ ኢትዮጵያዊያን ላይ የደረሰው አሰቃቂ ግድያ የዚህ ማሳያ ነው፡፡ የችግሩ መንስኤ ምንድነው? ማን ነው ተጠያቂው? እንዴትስ ማስወገድ ይቻላል? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት እና በመወያየት እንዲሁም የመፍትሔ ሃሳቦችን በማመንጨት ችግሩን ከመሰረቱ ለማድረቅ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋሟት ብዙ ይጠበቃል፡፡

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተለያዩ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ብሄር እና የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች የሚመሩበት እና ሃሳብ የሚለዋወጡበት መድረክ ናቸው፡፡ ይህ ልዩነት ባለበት ሁኔታ ሠላማዊ ሁኔታን መፍጠር ከተቋማቱ ይጠበቃል፡፡ የተማሪው ማሕበረሰብ ሴኩላሪዝምን / ከፖለቲካና ከሀይማኖት ነፃ የሆነ አስተሳሰብ/ በመተግበር እና መቻቻልን በማጎልበት ሽብርተኝነትን ከስሩ ማድረቅ ይቻላል፡፡

ሁሉም ባለው የባህል፣ የቋንቋ፣ የሐይማኖት፣ የዘር፣ የፓለቲካ እና የአስተሳሰብ ልዩነቶችን አቻችሎ እንዲሁም የግልና የጋራ በሚያደርጉ ሁኔታዎችና አመለካከቶች ላይ በመስማማት ለሐገር የሚጠቅም ሥራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የነፃ አስተሳሰብ መድረኮች ናቸው፡፡ በእነዚህ ተቋማት የሚማሩና ነገ ተመርቀው ለሐገራቸው እድገት እና ብልፅግና መሰረት የሚጥሉ ተማሪዎች ማፍለቂያ በመሆናቸው ነፃ አስተሳሰቦችን በሰላማዊ መንገድ እንዲያንፀባርቁ እና መቻቻልን እንዲያዳብሩ የዩኒቨርሲቲ አመራሮች፣ መምህራን እና የአስተዳደር ሰራተኞት በጋራ በመሆን መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አንፃር የኛ ኃላፊነት ምንድነው? የምሁራን ሚና ምንድነው? ምን ዓይነት አቅጣጫ መከተል አለብን? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት መወያየት፣ ሙሁራዊ ትንተና መስጠት እና የመፍትሔ ሃሳቦችን ማመንጨት እንዲሁም በተገኘው መድረክ ሁሉ ስለ መቻቻል እና ስለ ሰላም መስበክ አስፈላጊ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል እንላለን፡፡

**እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!**

## ቁልፍ መልዕክት

### የማህበረሰብ ዕድገት በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

በዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ውስጥ የማህበረሰብ ዕድገት ምንድን ነው? ይህ ዕድገትስ እንዴት ይመጣል? ከዚህ አንፃር በአለም ላይ ያሉ ተጨባጭ ልምዶች ምን ያስተምራሉ? ከኢትዮጵያ ሁኔታስ ምን እንማራለን? ወዘተ. የሚሉ ጥያቄዎች ተደጋግመው ይነሳሉ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች መነሳታቸው በራሱ ትልቅ ዕድገት ነው፡፡ የዚህ አጭር ጽሑፍ አላማ የተወሰኑትን ከዩኒቨርሲቲው ተልዕኮ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሀሳቦች በማንሳት የማህበረሰባችንን ውይይት ለማጠናከር ነው፡፡

የማህበረሰብ ዕድገት የሚለውን ሀሳብ የገቢ ማደግን፣ የጤናና የትምህርት ደረጃ መሻሻልን ባቀፈ አግባብ መግለጽ ይቻላል፡፡ በዚህም መሰረት መልኩ የማህበረሰብ ዕድገት ስንል የምናነሳው ጉዳይ የነዚህ ማህበረሰብ ገቢ የመሻሻል ሁኔታን፣ የጤናቸውና የትምህርት ሁኔታቸውን ያቅፋል ማለት ነው፡፡ በራዕይ ጥበብ 2017 የማህበረሰብ ዕድገት እናመጣለን ስንል በምናስመርቃቸው ተማሪዎች ስራ፣ በምርምር ያገኘነውን ውጤት ተግባር ላይ በማዋልና ከተለያዩ ምንጮች የሚገኝ ዕውቀትና ክህሎት ወደ ማህበረሰቡ በማሸጋገርና ተግባር ላይ እንዲውሉ በማሳለጥ የማህበረሰቡ ዕድገት እንዲመጣ እናድርግ ማለታችን ነው፡፡ ስለሆነም እንደ ዩኒቨርሲቲ፣ እንደ ኮሌጅ፣ እንደ ት/ቤትና እንደ ትምህርት ክፍል የሁላችንን ሚና ከዚህ አኳያ መመዘን ይገባል፡፡

ከተመራቂዎቻችን ብንጀምር እስካሁን ያስመረቅናቸውን ተመራቂዎች ባናስመርቅ ኖሮ ልናጣው የምንችለው የህብረተሰብ ዕድገት ምን ይሆን ነበር? እስከ አሁን በምርምር ያሳተምናቸው ህትመቶች ባይታተሙ ኖሮ ምን አይነት የማህበረሰብ ዕድገት እናጣ ነበር? እስከ አሁን የሠራናቸውን የማህበረሰብ አገልግሎት ባንሠራቸው ኖር ምን ጉድለት ይኖር ነበር? ወዘተ. ብለን በየዘርፎቻችን ብንወያይ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ እንዲህ አይነት ጥያቄዎች ትምህርትን በተግባር ከማዋል አኳያ ያሉብንን ክፍተቶች የሚሞሉበትን አግባብ ለመቀመር ያግዛሉ፡፡ በጥልቀት ከተወያየን አንድ መምህር ክፍል ገብቶ አንድ ክፍለ ጊዜ የሚያስተምረው/የምታስተምረው ትምህርት ከማህበረሰብ ዕድገት አኳያ እንዴት ይተረጐማል እስከሚለው ድረስ ልንደርስ እንችላለን፡፡

በዚህ መሠረት ሁሌ የምንሠራቸውን ስራዎች ከማህበረሰብ ዕድገት ጋር የማቆራኘት ደረጃ ላይ እንደርሳለን ማለት ነው፡፡ በዚህ አግባብ አንድ የኬሚስትሪ ተማሪ ስለ ኬሚካሎች ኡደት ሲማር/ስትማር ወዲያውኑ የጠላንና የአረቄን አሠራር ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ለመረዳት ይሞክራል/ትሞክራለች፡፡ በዚህ ያለውን ዘርፍ መረዳት ብቻ ሳይሆን ሂደቱ የሚሻሻልበትንና ውጤታማ የሚሆንበትን መንገድ ሲቀምሩ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ገቢን የሚጨምር አሠራር ስለሚፈጠር ዕውቀትም ገቢም ጨመረ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የጠላና የአረቄ አሠራር ቆሞ ቀርና ባለበት ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ሳይሆን ተከታታይ ትውልዶች እያሻሻሉት የሚሄዱት ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ ሂደት የማህበረሰብ ዕድገት ይረጋገጣል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ሀይልና ሙቀት የምትማር ተማሪ ዕውቀቱን እንደያዘች የምታስበው የእንጀራን አሠራር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ሙቀት እንዴት ይፈጠራል፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታስ እንዴት ይተላለፋል ወዘተ. የሚለውን እሳቤ ወስዳ አሁን ያለውን የእንጀራ አሠራር ጠንካራና ደካማ ጐን በመለየት አዲስ አሰራር ልትቀምር ትችላለች፡፡ ይህ አዲስ ቀመር ሲተገበር በቀላል ሀይል ብዙ እንጀራ የሚጋግር፣ ጭስ የሌለውና ጉልበት ቆጣቢ የሆነ በማህበረሰቡ ውስጥ ወጪ የሚቀንስ፣ ጤና የሚያሻሽልና በእንጀራ አሠራር ላይ አዲስ ትምህርት ስለሚገኝ ይች ሰው የማህበረሰብ ዕድገት የሚያመጣ ስራ ሰራች ማለት ነው፡፡

በአመራርና አስተዳደር ዘርፍም የሚማሩ ተማሪዎች ህዝብ በማቀናጀት ውጤት እንዴት ሊመጣ እንደሚችል ሲማሩ ወዲያውኑ ኢትዮጵያውያንን ወይም የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መምህራንን በማቀናጀት ውጤታማ ስራ መስራት የሚቻልበትን ስልት በመቀመርና ሀሳቡም እንዲወሰድ በማድረግ የማህበረሰብ ዕድገት ማምጣት ይቻላል ማለት ነው፡፡

የማህበረሰብ ዕድገት ስንል በራዕይ ጥበብ 2017 ምን ማለት እንደሆነና በምሳሌ እንዴት ሊገለጽ እንደሚችል በአጭሩ ቀርቧል፡፡ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብም ሀሳቡን በሂደት እያደበረው፣ ትርጉም ያለው ስራ እየሰራበት የሚሄድበት አማራጭ ያለ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ ነው፡፡

**ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!**

# አበይት ዜናዎች...

## የሳይንስ ኮሌጅ ዓመታዊ ጉባኤ አካሄደ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ኮሌጅ 3ኛውን ዓመታዊ ጉባኤ የሳይንስ ዕድልና ለዕድገት ያለው ሚና (prospects of Science and its Role for development) በሚል ርዕስ የሁለት ቀናት ጉባዔ አካሄደ።

በሊቢያና በደቡብ አፍሪካ ለሞቱት ኢትዮጵያዊያን የጋራ የህሊና ጸሎት በማድረግ የተጀመረው ጉባኤ የኮሌጁ ዲን ዶ/ር እሰዬ ከበደ ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ተከፍቷል። ጉባኤው መምህራን፣ ተመራማሪዎች፣ የዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የሚሳተፉበትና ሳይንስን ከማስተዋወቅ ረገድ በአገር ውስጥ ካሉ 21 ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ አንጋፋና ወጣት ተመራማሪዎች የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን የሚያቀርቡበት በመሆኑ ከፍተኛ የልምድ ልውውጥ እንደሚደረግበት ዶ/ር እሰዬ ገልጸዋል። በጉባዔው ስልሳ ሶስት (63) የምርምር ሥራዎች የቀረቡ ሲሆን ብዛት ያላቸው ጥናታዊ ጹሑፎች መቅረባቸው ብዙ አማራጮችን በማየት ወደ ተግባር ለመለወጥ እንዲያመች እንዲሁም ጀማሪ ተመራማሪዎች ልምድ እንዲቀስሙ ዕድል ለመፍጠር እንደሆነ ዶ/ር እሰዬ ተናግረዋል።

የኮሌጁ መምህራን ከመማር ማስተማሩ በተጨማሪ በምርምር፣ በማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ እንደሚገኙና የሚደረጉት ምርምሮችም በማህበራዊ፣ አካባቢያዊና በተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር ላይ ትኩረት ያደረጉ እንደሆኑ የኮሌጁ ዲን ገልጸዋል።

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ሳይንስን መሰረት ያደረገ ዕውቀትና ሀብት በመፍጠር አገሪቱን መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አውደ ጥናት አካሄደ

በሙሉጉጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ የህክምናና ተያያዥ አገልግሎቶችን ወጥነት ባለው መልኩ ለማከናወንና ለማሻሻል ከአጋር አካላት ጋር ለሁለት ተከታታይ ቀናት የምክክር አውደ ጥናት አካሄደ።

አውደ ጥናቱን በንግግር የከፈቱት የዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ ዩኒቨርሲቲው እያከናወናቸው ያሉ በርካታ አኩሪ ተግባራት ዘርዝረው ራዕዩን ለማሳካት ከመደበኛው የመማር ማስተማሩ ስራ ባሻገር ምርምር ላይ ትኩረት በማድረግ አበረታች ስራዎችን በመስራት ላይ እንዳሉ ገልፀዋል። ዶ/ር ማተቤ አያይዘውም ከአውደ ጥናቱ የህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትን በተመለከተ ጥሩ ግብዓት እንደሚገኝ ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል።

የአውደ ጥናቱ ዋና ዓላማ በህክምና ሙያ ላይ የሚሰጡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማሻሻል በር ከፋች የሆኑ ስራዎች የሚያቀርብበትና የእውቀት ሽግግር የሚደረግበት እንዲሁም ከሌሎች ተሞክሮ የሚወሰድበት እንደሆነ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ መምህር ዶ/ር ዘላለም ተመስገን ገልፀዋል።

በአውደ ጥናቱ ላይ በርካታ ምሁራን ስራቸውን ያቀረቡ ሲሆን የተነሱትን ሀሳቦችን ወደ ተግባር በመለወጥ የተሻለ የአሰራር ስርዓትን መዘርጋትና ከአጋር አካላት ጋር የተጀመሩ ግንኙነቶች በይበልጥ መጠናከር እንዳለባቸው ተሳታፊዎች ተናግረዋል። ከተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ምሁራንና ተመራማሪዎች እንዲሁም ከሚመለከታቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶች ጥሪ የተደረገላቸው ባለሙያዎች በአውደ ጥናቱ ላይ ተሳትፈዋል።

## የአማርኛ ቋንቋና የባሕል ዘርፎች 3ኛው አገር አቀፍ ዓውደ ጥናት ተካሄደ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ የአማርኛ ቋንቋና የባሕል ዘርፎች 3ኛውን አገር አቀፍ ዓውደ ጥናት አካሄደ።

በመክፈቻ መርኃ ግብር ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር ስዩም ተሾመ ፋኩልቲው የተለያዩ ምርምሮችን እያካሄደ እንደሚገኝ ገልጸው አማርኛ ቋንቋ የአገሪቱ የስራ ቋንቋ በመሆኑ በምርምር በመደገፍ ቋንቋውን ማሳደግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። በፋኩልቲው የሚገኙት የአማርኛና የፎክሎር ትምህርት ክፍሎች በየዓመቱ እያካሄዱ ያሉት ይህን አውደ ጥናት ወደፊትም አጠናክሮ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት ተካሄደ

በአበባ ሐብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አስተዳደርና ልማት ጥናት ትምህርት ክፍል ዲሞክራሲ ለዘላቂ ልማት "Democracy for sustainable Development" በሚል መሪ ቃል ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ።

አውደ ጥናቱን በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የከፈቱት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ዩኒቨርሲቲውን በአፍሪካ ውስጥ ጥናትና ምርምር የሚደረግበት ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ መምህራን የሚያስፈልገውን ግብአት በማቅረብና ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር ለመስራት ጥረት እያደረገ ይገኛል ብለዋል። አውደ ጥናቱም አጋር አካላትንና ተመራማሪዎችን በማገናኘት እንዲወያዩና አብረው

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት ለሴት ተማሪዎች የማማከር ስልጠና ሰጠ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት ለ30 ሴት መደበኛ ተማሪዎች የማማከር (የሜንተርሺፕ) ስልጠና ሰጠ።

በመርኃ ግብሩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክተር ወ/ሮ እንዳስ ቃሶ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ከማሕበራዊ፣ ከስነ-ልቦናዊ እና ከስነ-ተዋልዶ ጋር ተያይዞ ብዙ ችግሮች ሲያጋጥማቸው ወዴት መሄድና ለማን ማማከር እንዳለባቸው እንኳን ግንዛቤ የሌላቸው ሴት ተማሪዎች መኖራቸውን ጠቁመው የማማከር (የሜንተርሺፕ) ስልጠናው በዚህ ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የተዘጋጀ መሆኑን ገልፀዋል።

የስልጠናው ዋና አላማ ስልጠናውን የወሰዱ ተማሪዎች ሌሎች ሴት ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በአግባቡ በመፈተሽና በመለየት እራሳቸውንና ጓደኞቻቸውን ለመጠበቅና መከላከል የሚያስችላቸው እንዲሁም ለሌሎች አርአያ በመሆንና የምክር አገልግሎት በመስጠት ለስኬት ለማብቃት መሆኑን ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

ሰልጣኞቹ ከአራት ግቢዎች የተውጣጡ በትምህርታቸው ጥሩ ውጤት ያላቸው፣ በስነ ምግባር የተመሰገኑና በበጎ ፍቃደኝነት መስራት የሚፈልጉ ሴት ተማሪዎች ናቸው። ስልጠናው በራስ መተማመን፣ አርአያ መሆን፣ ችግር ፈች፣ ደስተኛ፣ ከራስ አልፎ ሌሎች ሰዎችን መርዳት እንዴት እንደሚቻልና ሌሎች ሴት ተማሪዎችን ከአደጋ እንዴት መታደግና እራሳቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ግንዛቤ እንደፈጠረላቸው ሰልጣኞች ተናግረዋል።

## የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም የምስረታ ጉባዔ ተካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም የምስረታ ጉባኤ ተካሄደ። በምስረታ ጉባኤው ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ዩኒቨርሲቲው እውቀትን ለመጠበቅ፣ ለመጠቀም እና ለማስተላለፍ እንዲሁም ህብረተሰቡ እንዲጠቀምበት ለማድረግ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ አንድ ሳምንት ተመርጦ የንባብ ሳምንት ብሎ በመሰየም ማህበረሰቡ እንዲያነብና እንዲፅፍ ለማድረግ እንደሚሰራ ተናግረው መገናኛ ብዙሃንም በሚያሰራጯቸው መርሃ ግብሮች የአማርኛ ቋንቋን መደበኛነት ጠብቀው እንዲናገሩና እንዲፅፉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## ካስኬፕ ፕሮጀክት የምክክር መድረክ አካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

በተግባር የተረጋገጡ መልካም የግብርና ተሞክሮዎችን ለማስፋፋት የአቅም ግንባታ በኢትዮጵያ (Cascape) ፕሮጀክት የምግብ ገብስ፣ የሮደስ ሳርና የጣፋጭ ግብጦ የማስፋፋት ሙከራና የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎና ሚና በሚል የምክክር መድረክ በዳንግላ ከተማ አካሄደ።

በምክክር መድረኩ ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያስተላለፉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማሕበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ዶ/ር ጌታቸው ፍስሐ የካስኬፕ ፕሮጀክት የዩኒቨርሲቲውን ገፅታ በመገንባትና የአርሶ አደሩን ህይወት በእጅጉ በመቀየር አስተማማኝ የሆነ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ገልጸዋል።

በዩኒቨርሲቲው የግብርና እና አካባቢ ሳይንስ መምህርና የፕሮጀክቱ አስተባባሪ ዶ/ር ይሽነዉ ገ/ሥላሴ እንደገለጹት ፕሮጀክቱ ከ5 ዓመት በፊት በአንድ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# አበይት ዜናዎች...

## ዩኒቨርሲቲው ከሱዳኑ አልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ

በሙሉጎጃም አንዱአለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከሱዳኑ አልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ፡፡ ስምምነቱን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤና የአልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ ምክትል ቻንስለር/ፕሬዚዳንት/ ፕሮፌሰር ሲሃም ሙሐመድ ተፈራርመዋል፡፡ ስምምነቱ በሁለቱ ዩነቨርሲቲዎች መካከል በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በተማሪዎችና መምህራን ልውውጥ ላይ አብሮ ለመስራት የሚያስችል መሆኑ ተጠቁሟል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ዩኒቨርሲቲው ከአልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ ጋር አብሮ ለመስራት ያለውን ቁርጠኝነት ገልጸው ስምምነቱ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥና በሁለቱ ዩኒቨርሲቲዎች ያለውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የአልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ ምክትል ቻንስለር ፕሮፌሰር ሲሃም ሙሐመድ በበኩላቸው እንደተናገሩት በሁለቱ እህትማማች ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የሚደረገው የልምድ ልውውጥ ግንኙነቱን የበለጠ እንደሚያጠናክረው ገልጸዋል፡፡ ፕሮፌሰር ሲሃም ዩኒቨርሲቲያቸው ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር ለመስራት ያለውን ፍላጎት ገልጸው ስምምነቱን በስራ ላይ ለማዋል እንደሚጥሩ ተናግረዋል፡፡

የአልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ትብብር ዳይሬክተር ዶ/ር አሽራፍ ኢዘለዲን ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ዩኒቨርሲቲያቸው ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር አብሮ ለመስራት ስምምነት ማድረጋቸው ምክንያቱ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ባስመዘገበው ስኬትና ውጤት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በስምምነቱ ላይ ሁለቱም ዩኒቨርሲቲዎች ስኬቶቻቸውንና ጥንካሬዎቻቸውን እንዲሁም ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶችና የተወሰዱ መፍትሄዎችን አቅርበዋል፡፡ በውይይቱ ወቅት የሱዳኑ አልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ በህክምናው ዘርፍ እንዲሁም ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በባዮቴክኖሎጂ ልምድ ስላላቸው በዘርፎቹ አብሮ ለመስራት ተስማምተዋል፡፡ በስምምነቱ ወቅት ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ ዳይሬክተሮችና ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የመጡ ጋዜጠኞች ተሳትፈዋል፡፡

## ለኢንዱስትሪ ዕድገት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሀላፊነት እንዳለባቸው ተገለፀ

በየማነ ገብሩ

ለጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ጥሬ እቃ በአገር ውስጥ በጥራት እንዲመረት በማድረግ፣ ዘርፉን በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማስቻልና ምርቱን ለማሳደግ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጐላ ድርሻ መጫወት እንዳለባቸው ተገለፀ፡፡ ይህ የተገለጸው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅና ፋሽን ዲዛይን ቴክኖሎጅ ተቋም ለ4ኛ ጊዜ ከሚያዝያ 23-24/2007 ዓ.ም cotton, textile and apparel value chain in Africa በሚል መሪ ቃል ባዘጋጀው አለም አቀፍ ጉባዔ ነው፡፡

አለም አቀፍ ጉባዔውን የከፈቱት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በተቋሙ ተምረው የሚመረቁ ተማሪዎች በእውቀትና በክህሎት ታንጸው በአለም አቀፍ ደረጃ ባሉ ግዙፍ ፋብሪካዎች ተወዳዳሪ ሆነው በመቀጠር ያገኙትን እውቀት፣ ክህሎትና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ልምድ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## ተቋሙ አለም አቀፍ ጉባዔ አካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ተቋም 3ኛውን አመታዊ ጉባዔ The Advancements of Science and Technology በሚል መሪ ቃል በተቋሙ የመሰብሰቢያ አዳራሽ አካሄደ፡፡

የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ም/ፕሬዝዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ ለ3ኛ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

## የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዝዳንቶች ክርክር አካሄዱ

በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ቻንስለሮች (vice chancellors) “Secularism and politicized faith in Africa” በሚል ርዕስ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ክርክር አካሄዱ፡፡ በእለቱ ለእንግዶችና ለተሳታፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ለውይይት የቀረበው ርዕስ ወቅታዊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ስለ ሴኩላሪዝም የተለያዩ ሀሳቦችን ሰፋ አድርገው የዘረዘሩት በሚንስተር ማዕረግ የጠቅላይ ሚንስትሩ ልዩ አማካሪና የጣና ፎረም ምክትል ሊቀመንበር የተከበሩ ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ ናቸው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ ሽብርተኝነት ለመከላከል የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንቶችና የፖለቲካ መሪዎች በጋራ አብሮ መስራት ወሳኝ መሆኑን የገለጹት ደግሞ የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዚዳንትና የጣና ፎረም ሊቀመንበር ኦለሲጉን ኦባሳነጆ ናቸው፡፡ እንደሳቸው ገለፃ የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች በአህጉሪቱ በተለይ ደግሞ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሽብርተኝነት ሃሳብ ከማስወገድ አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡

በክርክሩ ላይ የተሳተፉት ፕሬዚዳንቶች ሽብርተኝነት በአህጉሪቱ ላይ እያስከተለ ያለውን አደጋ ላይ ትኩረት ሰጥተው የተወያዩ ሲሆን ችግሩን ለማስወገድ የዩኒቨርሲቲዎች ሚና ምን መሆን እንዳለበት በዝርዝር አቅርበዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እንደገለፁት የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ሚና ሊሆን የሚገባው የባሕል፣ ሀይማኖትና ብሄር ልዩነቶችን በመገንዘብ ግጭትን መፍታት ነው፡፡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር አማሱ ፀጋዬ በበኩላቸው የብዙ ቋንቋዎችና የተለያዩ ብሄረሰቦች መገኛ የሆኑት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ከሀይማኖት ነፃ የሆነ አስተሳሰብን መተግበር አስቸጋሪ ቢሆንም የአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ሁኔታውን በመቆጣጠርና በመምራት መፍታት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

ችግሩን ለመፍታት ስነ ምግባርን ማስተማር ከዩኒቨርሲቲዎቹ እንደሚጠበቅ የገለፁት ደግሞ የአላሳኔ ኦታራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ላዛሬ ፓም ናቸው፡፡ የዌስትርን ኬፕ ዩኒቨርሲቲ ም/ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ቪቬን ላዋክ ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎች የብዝሃነት፣ የብሄርንና የሀይማኖት አስተምሮቶች በተማሪዎች ላይ መስረፅ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎቻቸውን በልዩነታቸው ላይ በግልፅ እንዲወያዩ በማድረግ በአለም ዙሪያ ተመራጭ ምሩቃን እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚቻል በተጨማሪ ገልፀዋል፡፡

የጁባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ጆን አፑሩ አኬክ በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲዎች አብሮነትና የተለያዩ ሀሳቦችን በግልጽ እንዲንሸራሸሩ በማድረግና ስለሰላም በማስተማር ችግሩን መቅረፍ እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡ የአልሀዚም አልዛሀር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ሲሀም ሞሀመድ እንደገለፁት ማሕበረሰብ ተኮር ስርዓተ ትምህርት በመቅረፅና ከተለያዩ የመንግስት ቢሮዎች ጋር በጋራ በመቀናጀት ሽብርተኝነትን መዋጋት ይቻላል፡፡ ፕሬዝዳንቶቹ በኬንያ ጋሪሳ ዩኒቨርሲቲ የአልሸባብና በሰሜን ናይጄሪያ ከ300 በላይ ሴቶችን ያገተው የቦኮ ሀሪም የሽብርተኝነትን ድርጊት በጥብቅ አውግዘዋል፡፡

በእለቱ “Secularism as an antidote to fundamentalism and violence” በሚል ርዕስ የ Tunisia’s Main Islamist Ennahda movement መሪ በመሆኑት በሚስተር ሼክ ራቺድ አልጋኖሺ ገለፃ የተደረገ ሲሆን ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡

## ዩኒቨርሲቲው ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ

በትዕግስት ዳዊት

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲና የኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ፡፡ ስምምነቱን የተፈራረሙት የዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ እና የኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሙሴ ያዕቆብ ናቸው፡፡

ዶ/ር ሙሴ በፊርማው ስነ ስርዓት እንደገለጹት የደራሲያን ማሕበር ከተቋቋመ 55 አመት እንደሆነው ገልጸው ዓላማውም አንባቢ ትውልድ በመፍጠር የንባብ ባሕልን ማዳበር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የማሕበራዊ ድህረ ገፆች መብዛት ለንባብ ባሕል አለመዳበር ምክንያት እየሆነ በመምጣቱ ማህበሩ በቂ መፅሀፎችን በመፃፍ አንባቢዎችን ለመሳብ እየሰራ እንደሚገኝ አክለው ተናግረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር በስነ ፅሁፍና በቋንቋ የባሕል ማዕከላትን በማቋቋም ባሕልንና የቋንቋ እድገትን ከማፋጠን አንፃር ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር እየሰራ መሆኑን ዶ/ር ሙሴ ገልጸው ከአንጋፋውና ብዙ የስነ ፅሁፍ ባለሙያዎችን ካፈራው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር የመግባቢያ ስምምነት መፈራረሙ ለማህበሩ ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ ከኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር ጋር የአጋርነት ስምምነት መፈራረሙ እንዳስደሰታቸው ገልፀው በዩኒቨርሲቲው የቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም መመስረቱ በቋንቋና በስነ ፅሁፍ ላይ ምርምር ለማካሄድ አስተዋጽኦ እንዳለው እንዲሁም የዩኒቨርሲቲውን ባሕል ማዕከል በማሳደግ ረገድ የደራሲያን ማሕበሩ ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ የንባብ ባሕልን ለማዳበር በጋራ መስራት እንዳለባቸው ከአደራ ጋር መልዕክት ያስተላለፉት ዶ/ር ፍቅረሰላም ስምምነቱ ለሀገር ትልቅ ስራ ለመስራት ግብአት የሚገኝበት በመሆኑ ከፊርማ በዘለለ ተግባር ላይ እንዲውል ሁለቱም ተቋሞች ጠንክረው መስራት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል፡፡

በስምምነቱ ላይ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማሕበር አባላት፣ መምህራንና ጋዜጠኞች የተሳተፉ ሲሆን ስምምነቱን አስመልክቶ የየራሳቸውን ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከመጋቢት ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ

ከዚህ በፊት ተማሪ ተስፋሁን በስርቆት ወንጀል ተጠርጥሮ በፖሊስ ጣቢያ በቁጥጥር ሥር ውሎ ጉዳዩ በመጣራት ላይ ቢሆንም እሱ ግን ከነገ ዛሬ እወጣለሁ በሚል ተስፋ ከትምህርቱ ወደ ኋላ መቅረቱ አሳስቦት ጓደኞቹ ያመጡለትን መጻሕፍትና ሌሎች አጋዥ ጽሑፎች በማንበብ ለመረጋጋት እየሞከረ እንደሆነ እናስታውሣለን፡፡ ቀጣዩን ሁኔታ ለማወቅ ደግሞ አብረን እንከታተለው ......................

ፍርድ ቤት ቀርቤ በጊዜ ቀጠሮ እንድቆይ ከተደረገ በአምስተኛው ቀን ከሰዓት በኋላ መርማሪው ፖሊስ ጠራኝና ‹‹ለምን እውነቱን አትናገርም›› በማለት እንደገና ጠየቀኝ፡፡ እኔም ‹‹ምን ብዬ እንደምነግርህ አይገባኝም! በምንም ተአምር የሥርቆት ተግባር አልፈፀምኩም፡፡ አስተዳደጌም እንደዚህ ዓይነቱን ተግባር እንድፈፅም አይገፋፋኝም፡፡ ይልቅስ እባክህ ትምህርቴን አቋርጬ በከንቱ እዚህ ጊዜዬን እንዳላጠፋ ልፈታ›› በማለት ተማጸንኩት፡፡ እሱ ግን ከጉዳይም አልጻፈኝም፡፡ እንዲያውም ‹‹አትቀልድ እውነቱን በመናገር ጊዜህን በከንቱ ሳታባክን ተገቢውን ውሳኔ ብታገኝ ይሻልሃል፡፡›› በማለት አንገቱን ደፍቶ ይጽፍ ጀመር፡፡

እኔ ከመርማሪው ፖሊስ ጋር እያለሁ ሁለት ፖሊሶች ሦስት ወጣቶችን ይዘው በመምጣት ፖሊሳዊ ሰላምታ ሲሰጡት የእኔን ጉዳይ ችላ በማለት አትኩሮቱን ወደ እነሱ በማድረግ እኔን እንድወጣ ትዕዛዝ ሰጠኝ፡፡ ያለምንም እልባት ወጥቼ ሄድሁና ከእሥረኛ ጠባቂው ፖሊስ ዘንድ በመቀመጥ ማንበቤን ቀጠልኩ፡፡

አሁን አሁን ጠባቂ ፖሊሶች እየተግባቡኝ መጥተዋል፡፡ ይሄኛው ፖሊስ የርቀት ትምህርት ስለሚማር የሚነበብ ማተሪያል ከእጁ አይለይም፡፡ በዚህም የተነሣ አልፎ አልፎ ያልገባውን ነገር እንዳስረዳው ይጠይቀኛል፡፡ እኔም የተቻለኝን እየረዳሁት ነው፡፡ በተለይ የሒሳብ ትምህርት እንደማይሆንለት እየተማረረ ይነግረኛል፡፡ እኔም የትኛው እንደሚቸግረው በመጠየቅ ሞጁሉን እንዲያመጣ ጠየኩት፡፡ ስመለከተው ቆየሁና በቀላል መንገድ የሚሠራበትን ዘዴ ሣሣየው ራሱን ችሎ መሥራት በመጀመሩ ደስ እያለው መጣ፡፡ ግልፅ እየሆነለት ሲመጣ ‹‹ራሴን ሰነፍ አድርጌ እየተመለከትሁ ነው እንጅ ለካንስ ቀላል ነገር ኖሯል፡፡›› እያለ መሥራት ያዘ፡፡ በመካከሉ የሚያስቸግረውን ሲጠይቀኝ እንዴት እንደሚሠራ ምሳሌ በመስጠት አስረዳዋለሁ፡፡ በዚህ ሁኔታ በጣም እየተቀራረብን ስለመጣን ሌሊትም እዚያው ከእነሱ አጠገብ እንድተኛ ስለተፈቀደልኝ ከቁንጫ፣ ከትኋንና መሰል ተባዮች በቀላሉ ተገላገልሁ፡፡

አንድ ቀን ልክ ስድስት ሰዓት ተኩል አካባቢ ምሣ ከበላን በኋላ አንድ ወጣት እሥረኛ መጣ፡፡ ወዲያው ቀደም ብሎ ታሥሮ የሰነበተ አንድ እሥረኛ አዲስ ገቢውን ‹‹እንኳን ደህና መጣህ›› አለና ቀስ ብሎ ቀርቦ ሲያናግረው ቆዩ፡፡ በመቀጠልም በሚለዋወጡት ኃሳብ አለመግባባት እየተፈጠረ ስለመጣ እርስ በእርስ ድብድብ ጀመሩ፡፡ ከዚያ አጠገባቸው ያሉ እሥረኞች በመሃል ገብተው ሲያገላግሏቸው በተለይ እዚህ የሰነበተው ፈርጠም ያለው እሥረኛ ‹‹ገንዘቤን ያለአግባብ ስለወሰደ ይመልስልኝ›› በማለት እንደገና ለመደባደብ ሲገለገል ሌላኛው ደግሞ ‹‹ያለአገባብ አይደለም ወዶ ነው የገዛኝ፡፡ ዛሬ እዚህ ስላገኘኝ አጋጣሚውን በመጠቀም ገንዘብ ለመቀበል ያመጣው ዘዴ ነው፡፡›› በማለት በበኩሉ በጉልበት መከላከል ቢያቅተውም በሀሳብ መከላከል ጀመረ፡፡

ፍርድ ቤት ቀርቤ በጊዜ ቀጠሮ እንድቆይ ከተደረገ በአምስተኛው ቀን ከሰዓት በኋላ መርማሪው ፖሊስ ጠራኝና ‹‹ለምን እውነቱን አትናገርም›› በማለት እንደገና ጠየቀኝ፡፡ እኔም ምን ብዬ እንደምነግርህ አይገባኝም! በምንም ታምር የሥርቆት ተግባር አልፈፀምሁም፡፡

ከዚያም ከእሥረኞች መካከል ትንሽ ምራቃቸውን ዋጥ ያደረጉት ነገሩን በሽምግልና ለማየት ካረጋጓቸው በኋላ ጉዳዩን በጥሞና እንዲያስረዱ ተደረገ፡፡ ተበደልሁ ባዩ ‹‹ይህን ካርድ መታወቂያ ነው ብሎ ሸጦልኝ ነበር፡፡ ነገር ግን የሸጠልኝ መታወቂያ ሳይሆን የምግብ ካርድ በመሆኑ ምንም ሣልጠቀምበት ቀርቻለሁ፡፡ እንዲያውም ይህን መታወቂያ ይዤ ወደ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ልገባ ስል ዋናውን መታወቂያህን አምጣ በማለት ዘበኛው ገላምጦ አባሮኛል፡፡›› ሲል ሸጠ የተባለው ደግሞ ‹‹በዚያን ጊዜ ከሁለት መታወቂያዎች መካከል ራሱ ፈልጎ መርጦ ነው የገዛው፡፡›› አለ፡፡ በመቀጠልም ‹‹ያን ጊዜ ደስ ብሎህ ስትመርጠው በዚህስ ምግብም መብላት ስለምችል ይህ ይሻለኛል አላልክም ነበር?›› በማለት ተከራከረ፡፡ ከዚህም በመነሣት ነገሩን ለማብረድ ሁለቱ እንዲደራደሩ ተደረገና ግማሽ ገንዘብ እንዲመልስለት ፍርድ ተሰጥቶ ካርዱን መለሰለት፡፡

ይህንን ሲከታተል የቆየ አጠገቤ ያለው እሥረኛ እኔን ቆንጠጥ አደረገኝና ጆሮዬን ወደ እሱ ጠጋ አድርጌ ሳዳምጠው ‹‹ለእኔ ሽጥልኝ ልበለው?›› አለና ወዲያው ‹‹ስማ ማነህ? ወንድሜ ለምን ለእኔ አትሸጥልኝም?›› አለው፡፡ ልጁም ወደ እሱ እየተመለከተ ምንም ሳያቅማማ ‹‹መግዛት ትችላለህ›› አለና ሰጠው፡፡

ከዚያም ተቀበለና ሲመለከተው እኔም አብሬ ሣየው ፎቶው ተገንጥሏል፡፡ ወረድ ብዬ ስሙን ሳነበው ማመን አልቻልኩም፡፡ የእኔው የምግብ ካርድ ነው፡፡ ሁኔታዬን ሲያይ እንድረጋጋ እንደገና ቆንጠጥ ሲያደርገኝ ተያየንና በቀላሉ ተግባባን፡፡ ወዲያው እንደገና አተኩሮ ሲያየው ቆዩና ‹‹እኔ እንኳን የምፈልገው የፖሊ ግቢን ነበር፡፡ ስለዚህ አይሆነኝም›› አለው፡፡ ሻጩም ‹‹ምን ችግር አለው አንድ ዩኒቨርሲቲ ስለሆነ ለሁሉም ያገለግላል፡፡ ›› በማለት ሊያግባባው ሞከረ፡፡ እሱ ግን ለሁሉም ይዞኸው ቆይ በማለት መለሰለት፡፡ ከዚያም እኔን የምታነብ መስለህ ውጣና ሁኔታውን ለፖሊሱ ንገረው አለኝ፡፡ እኔም ወደ በሩ በመጠጋት ፖሊሱ እንዲከፍትልኝ ምልክት ስሰጠው ከፈተልኝና ሁኔታውን ዘርዘር አድርጌ ሳስረዳው ስለሁኔታው ከእኔ ጋር አብሮ የሚመገበውን እሥረኛ አስጠርቶ በድጋሜ አረጋገጠና ‹‹እንዳይቀደው ልግዛህ ብለህ ተቀበለው›› አለው፡፡

እሱም እሽ ብሎ ገባና በማረሣሣት ትንሽ ቆይቶ በመደራደር አምሳ ብር እንደሚገዛው ቃል ገብቶ ይቀበለዋል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ፖሊሱ ለመርማሪው ሁኔታውን ስላስረዳው ወደ እኔ መጣና ‹‹እርግጠኛ የአንተ መሆኑን አይተሃል?›› አለና ጠየቀኝ፡፡ እኔም ሙሉ በሙሉ ማረጋገጤን ነገርኩት፡፡ ከዚያም ጠባቂ ፖሊሱን ‹‹ሂድና የሸጠውን አምጣው›› ሲለው ጠባቂው ፖሊስም ‹‹ካርዱን የሆነ እሥረኛ ልግዛህ ብሎ እንዲቀበለው አድርጊያለሁ›› አለው፡፡

መርማሪ ፖሊሱም ትንሽ ጊዜ ሲያስብ ቆዬና ‹‹የተጣሉት እነማን ናቸው?›› በማለት ሲጠይቀኝ በስም እንደማላውቃቸው ስነግረው ‹‹በል አሁን ወደ ውስጥ ግባ›› በማለት እንድገባ አደረገኝ፡፡ ከዚያም መርማሪው ቆየት ብሎ በሩን ከፍቶ በመቆም ‹‹ቀደም ሲል ስትደባደቡ የነበራችሁ እነማን ናችሁ?›› በማለት ትኩረት በመስጠት ጠየቀ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ፀጥ ስላለ የሚናገር ጠፋ፡፡ ይሁን እንጅ ፖሊሱ ‹‹አትናገሩም?›› በማለት ቆጣ ብሎ ሲጠይቅ ካርዱን የሸጠው ሌባ ጣቱን ወደ ተደባዳቢው ጎረምሣ ጣቱን በመቀሰር ‹‹ጉልበተኛ ሆኖ የሚደባደበው እሱ ነው፡፡ ›› በማለት ተናገረ፡፡ መርማሪው ፖሊስም ‹‹በል ና አንተ ጥጋበኛ!›› አለና ክንዱን ይዞ ወደ ቢሮው ሄደና ለምን እንደሚደባደብ ሲጠይቀው እንዳልተደባደበ ካደ፡፡ ወዲያው ትንሽ ቆየት ብሎ ተደበደብሁ ያለውን አስጠራውና ለምን እንደደበደበው ሲጠየቅ ‹‹ገንዘቤን መልስ በማለት ነው ›› አለ፡፡ ‹‹የምን ገንዘብ?›› በማለት መርማሪው ሲጠየቀው ‹‹ቀደም ሲል የሆነ ዕቃ ሸጬለት ስለነበር ነው›› ብሎ ቃሉን ሰጠ፡፡ መርማሪውም ‹‹ምን ዓይነት ዕቃ ነው›› ሲለው ዝም አለና መሬት መሬት መመልከት ጀመረ፡፡ ወደ ተደባዳቢው ዞር ብሎ ‹‹ምን ዕቃ ነው የሸጠልህ?›› ብሎ ሲጠይቀው ‹‹መታወቂያ ካርድ›› ብሎ ተናገረ፡፡ መርማሪውም ‹‹እሽ አሁን ካርዱ የታለ?›› በማለት ሲጠይቅ ገዝቶት የነበረው እሥረኛ ፈጠን ብሎ ‹‹ለሌላ ሰው ሊሸጠው ሲስማማ ነበር›› በማለት ተናገረ፡፡

በመቀጠልም ከእኔ ጋር ምግብ የሚበላውን እሥረኛ አስጠራና ካርዱን ከማን እንደገዛው ጠየቀው፡፡ እሱም የነበረውን ሁኔታ በመዘርዘር አስረዳ፡፡

በመጨረሻም መርማሪው ጥያቄውን ወደ እኔ በማዞር ‹‹ይህ ካርድ የማን ነው?›› ብሎ ሲጠይቀኝ የእኔ መሆኑን አረጋገጥኩለት፡፡ ከዚያም ‹‹እነዚህን ሁለቱን ሰዎች ከአሁን በፊት ታውቃቸዋለህ?›› በማለት ጠየቀኝ፡፡ እኔም እንደማላውቃቸው ቃሌን ሰጠሁ፡፡ እንደገና እነሱንም ‹‹እናንተስ ታውቁታላችሁ›› ሲላቸው እንደማያውቁኝ ተናገሩ፡፡ ወዲያው ‹‹ፎቶውን ማን ነው የገነጠለው?›› ብሎ መርማሪው ጠየቀ፡፡ የሸጠው ‹‹እኔ ከእነ ፎቶው ነበር የሰጠሁት፡፡ የገነጠለው እሱ መሆን አለበት›› ብሎ በፍጥነት ሲናገር ተደባዳቢው እሥረኛ ‹‹አዎ ገንጥዬ የራሴን ፎቶ ለጥፌበት ነበር›› አለና ቃሉን ሰጠ፡፡ ፖሊሱም ‹‹የተገነጠለው ፎቶ የት አለ?›› በማለት ሲጠይቀው ፎቶውን መገንጠሉን እንጅ የት እንደጣለው እንደማያስታውስ ቃሉን ሰጠ፡፡

ከዚህ በኋላ ሌሎቻችን እንድንመለስ አደረገና ካርዱን የሸጠውን ብቻ አስቀርቶ ይመረምረው ጀመር፡፡ ወዲያው ካርዶችን የተቀበላቸው ከሌላ ኪስ አውላቂ ሌባ እንደሆነ አንደኛውን መታወቂያ እዚህ ከመግባቱ በፊት ለሌላ ሰው መሸጡን ተናገረ፡፡ ከዚያም ካርዶቹን እንዲሸጥ የሰጠውንና የመታወቂያ ካርዱን የገዛውን ሰው እንዲያሳይ ከሁለት ፖሊሶች ጋር አያይዞ ላከው፡፡

አዛዡ ሌሎች ፖሊሶችን ጠርቶ ወንጀለኞች ይገኙበታል በተባሉበት ቦታዎችና አካባቢዎች ሁሉ አድነው እንዲይዟቸው መመሪያ በመስጠት አሰማራቸው፡፡

**ይቀጥላል!!!**

# *"The ultimate promise of technology is to make us master of a world that we command by the push of a BUTTON." Volker Grassmuck*

**Yenus Nurie (Department of English Language and Literature)**

This paper illuminates two primary serious problems that recur again and again in the academic year. The major purpose of this reflection is; therefore, to illustrate and reflect on the depth of the problems and to suggest ways to overcome these problems as I personally believe that they require urgent and top attention.

It has been almost a year since I heard teachers complaining about the massive challenge of the duplicating machines that were broken every other week. As a result, I and my colleagues were unable to duplicate materials absolutely necessary to supplement teaching. Even though I was disgruntled with the matter, I stayed vigilant to avoid the problem by any means I could. However, thinking the problem on the side of my students for a long time, I always felt that my inability to handle the problem and assist my students may make me bear a share of a moral guilt for their failure. To my dismay, what disturbed me most was whenever I went there, I often heard the same boring response: "The machines are not working".

Although getting repairs done quickly might be somewhat challenging, for many reasons, I can only assume that the current trends and maintenance practices could contribute for the existing problem to be entrenched. During the academic year, there were several occasions that I failed to get my materials duplicated as the machines were not working properly, and even if one or two of them were working, I had to wait for many days until my turn. I was sick and tired of asking if the machines were working. While I was talking with some people, I asked the real source of the problem, and I was informed that repairers take too long time to fix the problem, for it is said that the technicians come from a limited company whose experts are always engaged with their own businesses.

By the way, I don't think that the management has no idea of how fast and when to respond to requests; however, I feel that it had to handle the problem by evaluating its working principles and considering other means of maintenance as the current trend mentioned above tends out to be ineffective to address the maintenance problem.

***BDU has become the largest in the history of the institution. It has grown to be the second largest university among higher education institutions in the country.***

The second theme of my reflection is related to my first real concern, which actually poses the university to launch a new dimension of systematic and electronic filing system, which could help access employees' profiles and promotions with faster and more accurate filing structure than the manual bulk paper system.

Needless to say, BDU has become the largest in the history of the institution. It has grown to be the second largest university among higher education institutions in the country. For example, the number of students and instructors has risen dramatically. More new faculties have been launched, which opened increased job duties that require more professional as well as technical skills. As a result, as the complexity of the university grows, the demand for launching technological infrastructure seems to be compulsory. In this regard, the university has implemented SIMS, which it is credited for. I personally appreciate the best efforts made by the university to launch this technology.

While I have been impressed with the successful implementation of this partner, which has helped me to efficiently accomplishing my job, I have also been outraged by the failed ones, and this inspired me to reflect on a specific fault that I observed that could be handled easily if the university launched similar technology infrastructure. In response to the announcement made by the university to complete the necessary requirements to obtain a housing benefit, I had to get my documents verified. Like the rest of the other teachers who were waiting for their turn to attest their files and get letters, I had to patiently spend much of my working hours at the record office.

In the mean time, all the record officers including those who came from the human resource management office to assist them were busy to serve in the best interest of instructors. Truly speaking, everyone was cooperative and helpful for the scores of customers lined up around the record office. However, as the documentations of the files were manual, and hence not systematic and manageable, it was too hard for the record officers to obtain the necessary data as soon as we need them. We had to wait for more and more of our time until we get letters at hand. My sense of concern is: therefore, while the university is exercising its best on a manual record system, we can make the current filing system easier and effective by utilizing the appalling use of technology.

In essence, the human resource management has to provide employees with the capacity to manage their life, yet any failure to serve employees in a fast and accurate system may be deemed a total disregard of the employer on their right to obtain their documents when they need them. Pedagogically, the unfair wastage of time in waiting for establishing their files was embarrassing, which hurts their professional identity as it erodes their zeal to work hard, uproots pessimism which in turn harms the education quality we are striving to attain.

On top of all these, we can never be competitive with the rest of the world unless we update our performance and adjust with the plausible settings of this dynamic world. Above all, using the electronic technology for documenting files provides multiple simultaneous accesses that help us to cope with problems associated with corruption and data inaccuracy. In short, given the wide range of complexities, the university has to consider the impact of launching electronic documentation for it is time saving, fast and efficient.

In a nut shell, I personally believe that these problems which all of the instructors experienced will absolutely affect the future professional ambitions of teachers in particular and the broad goals of the university in general. Let us not forget that teachers are entitled to work better in promising working conditions and the success or failure in the pursuit of Bahir Dar University largely depends on instructors' satisfaction where they are working day and night, and, this complex staff can work efficiently if the right working conditions are in place. Thus, the university management needs to consult instructors and establish favorable working settings to avoid problems that they have experienced during the academic year if we have to move forward beyond rhetoric.

# “ለእኔ የሚገባኝ የግቢ ሕይወት ማለት ራሳችንን ሆነን የምንኖር ከሆነ ለወደፊት መሰረት የምንይዝበትና የምንለወጥበት ነው።”

ተማሪ ብዙአየሁ ጠለለው

ተማሪ ብዙአየሁ ጠለለው ትባላለች። በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ የገጠር ልማት ት/ክፍል የ2007 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪ ስትሆን ከትምህርቷ ጐን ለጐን የተማሪዎች መማክርት በመሆን እየሰራች ትገኛለች። በቅርቡ የዩኒቨርሲቲው የሴት ተማሪዎች አምባሳደር ሆና በመመረጥ ከስርዓተ ፆታ አኳያ በርካታ ጉልህ አስተዋፅኦዎችን እንድታበረክት ሀላፊነት ተሰጥቷታል። የናይል ጋዜጣ ዘጋቢ ሙሉጎጃም አንዱአለም የተማሪዋን የሕይወት ተሞክሮ ለአናባቢያን ለማካፈል እንግዳ አድርጋ አነጋግራታለች። ቃለ መጠይቁን እንሆ!

ናይል፡- ብዙአየሁ ስለ ትውልድሽ፣ አስተዳደግሽና የቀድሞ የት/ት ሕይወትሽ ትንሽ አጫውቺን?

ብዙአየሁ፡- በደሴ ከተማ በ1986 ዓ.ም የተወለድኩ ሲሆን ያደኩት ከእናቴና ከሁለት ታላላቅ እህቶቼ ጋር ነው። ትምህርቴንም የተከታተልኩት በዚሁ ከተማ ሲሆን ከአፀደ ሕፃናት እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ “ተስፋ ድርጅት” በሚባል የበጐ አድራጐት ት/ቤት ነውየተማርኩት። ይህ ት/ቤት በእውቀትም ሆነ በስነምግባር የታነፅኩበት ስለሆነ አሁን ለደረስኩበት ደረጃ መሰረት የጣለልኝ ነው ብዬ አምናለሁ። የመሰናዶ ትምህርቴን ደግሞ “መምህር አካለውድ” በሚባል ት/ቤት ተከታትዬ ለጥሩ ውጤት በመብቃቴ ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተቀላቅያለሁ።

ናይል፡- ወደ ዩኒቨርሲቲ የመግባቱን እድል ባታገኚ ኖሮ ምን ትሆኚ ነበር?

ብዙአየሁ፡- ወደ ዩኒቨርሲቲ የመግባት እድል ባላገኝም ከትምህርቱ ዓለም እርቃለሁ ብዬ አላስብም። በሌላ መንገድ ትምህርቴን ለመማር እሞክር ነበር።

ናይል፡- እስካሁን ያስመዘገብሽው ነጥብ ስንት ነው?

ብዙአየሁ፡- እስካሁን ያለኝ አጠቃላይ ውጤት 3.91 ነው

ናይል፡- የአጠናን ዘዴሽ ምን ይመስላል?

ብዙአየሁ፡- ብዙ ጊዜ ወስዶ ከማንበብ ይልቅ በአጭር ሰዓት ውስጥ ሙሉ ትኩረት ሰጥቶ ማንበብ ይመቸኛል። በተቻለኝ መጠን ክፍል ውስጥ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት በንቃት እከታተልና ባለኝ ጊዜ ትኩረት ሰጥቼ አነባለሁ።

ናይል፡- የግቢ ሕይወትንና ትምህርትን እንዴት ትገልጪዋለሽ? ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርሽው ነገር ምንድን ነው?

ብዙአየሁ፡- ለእኔ የሚገባኝ የግቢ ሕይወት ማለት ራሳችንን ሆነን የምንኖር ከሆነ ለወደፊት መሰረት የምንይዝበትና የምንለወጥበት ነው። ይህ ካልሆነ ግን ራሳችንን የምናጣበት ሕይወት እንደሆነ አምናለሁ። ትምህርት ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ዋና ዓላማ ብለን የምንይዘው ስለሆነ ሙሉ ትኩረት መስጠት አለብን እላለሁ። ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ ብዙ ነገሮች ተምሬበታለሁ። ለምሳሌ ያህል ከሰዎች ጋር እንዴት መግባባት እንደሚቻል፣ ራስን በምን ዓይነት መንገድ መምራት እንደሚቻል፣ የገንዘብ አጠቃቀም ዘዴን፣ ማንኛውንም ስራ ማከናወን እንደምችል እንዲሁም በራስ የመተማመን ልምዴን አዳብሬአለሁ። ትኩረት ሰጥቼ ከሰራሁ ውጤታማ መሆን እንደምችል ተምሬአለሁ።

ናይል፡- በግቢ ቆይታሽ የመማር ማስተማሩን ሂደት በምን ዓይነት መልኩ ታይዋለሽ? የመምህራን ብቃትስ እንዴት ትገልጭዋለሽ?

ብዙአየሁ፡- የመማር ማስተማሩ ሂደት ጥሩ ነው። አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩም መምህራንና ተማሪዎች በጋራ በመተባበር ችግሩን መቀነስ እንደሚችሉና የኮሌጁ አመራር አካላት እገዛም እንደሚያስፈልግ ተገንዝቤአለሁ። የት/ክፍሉ መምህራን ያላቸውን ልምድና እውቀት ተጠቅመው የትምህርቱን ይዘት በሚገባ እንድንረዳው የሚያደርጉት ጥረት አበረታች መሆኑን እገልፃለሁ።

ናይል፡- የ2007 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲው የሴት ተማሪዎች አምሳሳደር ሆነሽ ተመርጠሻል ስትመረጭ ምን ዓይነት ስሜት ተሰማሽ? የአመራረጡ ሂደት(ዳኝነቱ) እንዴት ነበር?

ብዙአየሁ፡- የተሰማኝ ስሜት እጅግ ከፍተኛ ደስታ ነው። የአመራረጥ ሂደቱ በመጀመሪያ ለውድድር መቅረብ የሚፈልግ ተብሎ ምዝገባ ተካሄደና ከሁሉም ግቢ አወዳዳሪዎች በያዙት መስፈርት መሰረት 10 ተማሪዎች ተመልምለን የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለፃ ተደረገልን። ለውድድሩ ራሳችንን እንድናዘጋጅ ከተነገረን በኋላ የውድድሩ ዕለት የመረጥነውን



ተማሪ ብዙአየሁ ጠለለው የዩኒቨርሲቲው የሴት ተማሪዎች አምባሳደር

“

ከተማሪዎች ሕብረት ውስጥም የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ስለሆንኩ አንዳንድ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ከተማሪዎችና ከኮሌጁ አመራር አካላት ጋር በመወያየት የቻልኩትን ሁሉ እየሰራሁ እገኛለሁ። እነዚህንና ሌሎች ተግባራትን ሳከናውን የጊዜ አጠቃቀሜን ለማስተካከል የሚሰሩ ስራዎችን እንደ አስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል በማስያዝ ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ እየሰጠሁ እሰራለሁ።

”

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# “ይህን ትልቅ መስዋእትነት እየከፈለ ያለው የአካባቢው ሕብረተሰብ ነው።”

ዶ/ር ዋሴ አንተነህ



ዶ/ር ዋሴ አንተነህ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዳይሬክተር

> “ እንግዲህ እንደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ያደረግነው ይህን ጥናት ካጠናን በኋላ ለሚመለከተው አካል ጉዳዩን ማሳየትና ማስረዳት ነው። እኛን የሚመለከተንም ይኸው ነው። ያደረግነው መጀመሪያ የክልሉን መንግስት ማሳመን ነው። በዚህም የክልሉ መንግስት ሙሉ በሙሉ ጉዳዬ ነው ብሎ ይዞታል። ”

ናይል፡- በቅድሚያ ራስዎን ለአንባቢያን ቢያስተዋውቁ?

ዶ/ር ዋሴ፡- ዋሴ አንተነህ እባላለሁ። የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዳይሬክተር ነኝ። በተጨማሪ ጣና ላይ በተከሰተው የወተርአይሲ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ፎካል ፐርሰን ሆኜ እያገለገልኩ ነው። ዩኒቨርሲቲውን በመወከል ማለት ነው።

ናይል፡- በእንቦጭ (ወተርአይሲ) ዙሪያ ምርምር አካሂደዋል። ምርምሩን ለመስራት ምን አነሳሳዎ?

ዶ/ር ዋሴ፡- በርግጥ ምርምሩ ለአካዳሚክ ጠቀሜታ ታስቦ የተሰራ ሳይሆን ምርምሩ ይህን አረም ያለበትን ደረጃ ለማወቅ ያደረግነው ምርምር ነው። ይህንን ምርምር ያው በተደጋጋሚ የምናደርገው ነው። በአመት ሁለቴ ወይም ከዛ በላይ አረሙ ምን ይመስላል? አረሙ ያለበትን ስርጭትና አሁን ያለበትን ደረጃ የት እንደደረሰ ለማወቅ ጥናት እናደርጋለን። ያገኘነውን ውጤት ፖሊሲ ከሚቀርጹ ጋር ወይም ደግሞ ይህንን አረም በማስወገድ ስራ ከተሰማሩ ከክልሉ መንግስት ከተለያዩ ሴክተሮች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ኮሙዩኒኬት እናደርጋለን። ዋናው ሥራችን ምንድን ነው እኔ ብቻ ሳልሆን ከሌሎች ጋር በመሆን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አንድ የተዋቀረ ቲም አለ። በጋራ የተዋቀረ ቲም ወተር አይሲን ሪሰርች ኤንድ አዲቫይዘሪ ቲም (Waterhyceince Research and Advisory Team) ይባላል። ይህ ቲም በምርምርና በማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ስር ነው ያለው። ይህን ቲም እኔ ነኝ እየመራሁት ያለሁት። ይህ ቲም ከሌሎች ሴክተሮች ጋር ለምሳሌ ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ማሕበር (አመልድ) እና ከክልሉ ግብርና ምርምር የተውጣጡ ቡድኖች በየጊዜው እየሄደ አሰሳ ያደርጋል። ባለፈው ሳምንት ለምሳሌ ክረምቱ ከመግባቱ በፊት አረሙ ምን ይመስላል? በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማየት የሰርቬይ ስራ ይሰራል። ሁልጊዜ የሰርቬይ ስራ ይሰራል። ይህ ስራ የሚሰራው ደግሞ በቴክኒክ ቲሙ ነው ማለትም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲና በሴክተር መስሪያ ቤቶች የተዋቀረው ነው።

ናይል፡- ባጭሩ ስለምርምሩ ግኝት ይግለጹልን?

ዶ/ር ዋሴ፡- ግኝታችን እንደሚያሳየው ወተርአይሲ በአማርኛ እንቦጭ የምንለው በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ነው ጣና ላይ መኖሩ የታወቀውና የተገኘው። በ2005 ዓ.ም በተደረገው ጥናት 20,000 ሄክታር አካባቢ የሐይቁ ዳርቻ እንደተሸፈነ ታወቀ። በሐይቁ ዳርቻ 20,000 ሄክታር በእንቦጭ እንዳተያዘ ከተረጋገጠ ከ2005 ዓ.ም ኦክቶበር (ጥቅምት) ጀምሮ ሕብረተሰብን በማስተባበር ወደ ዘመቻ ተወጣ። በዛ ዘመቻ ወቅት ከ90 እስከ 95 በመቶ የሚሆነው አረሙ ተወገደ። በዚህም አረም ተወግዷል ተብሎ ትንሽ መዘናጋት ተፈጠረ። ከ2005 ዓ.ም ክረምት ጀምሮ 2006 ዓ.ም ሙሉ ዓመት ምንም የረባ እንቅስቃሴ አልነበረም። 2006 ዓ.ም ነሐሴ ላይ ወተር አይሲን ሪሰርች ኤንድ አዲቫይዘሪ ቲም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲና በሴክተር መስሪያ ቤቶቹ ተቋቁሞ አረሙ በሐይቁ ላይ ያለበትን ሁኔታ አጥንቶ እንዲያመጣ ተላከ። ይህም ቲም አረሙ ያለበትን ሁኔታ አጥንቶ ያመጣው ውጤት በወቅቱ ያሳየው ወደ 50,000 ሄክታር የሚሆነውን የሐይቁ ዳርቻ ተሸፍኗል። ይህንን ውጤት ለክልሉ መንግስት ነው ያቀረብነው። በቀጥታ የአማራ ክልል ፕሬዚዳንት በተገኙበት በ2007 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ በአስቸኳይ ሕብረተሰብ ለዘመቻ እንዲንቀሳቀስ አደረግን። አሁን በያዝነው ወር መጀመሪያ ላይ ይሄ የቴክኒክ ቡድን ወይም ጥናቱን አጥንቶ የሚያቀርበው ቡድን ለቅኝት (survey) ወጥቶ ነበር። በእውነቱ በጣም የመቀነስ አዝማሚያ አለው። የአካባቢው ሕብረተሰብ ብዙውን ቦታ አስወግዶታል። ግን የአረሙ ተፈጥሯዊ ባሕሪ ስለሆነ ትንሽም ብትኖር በሳምንት በሁለት ሳምንት በእጥፍ ይጨምራል። ስለዚህ በየጊዜው ክትትል የሚያስፈልገው ነገር ነው። ትርጉም ባለው ሁኔታ ቢቀንስም አሁን ደግሞ ክረምቱን ተከትሎ ደግሞ ሊከሰት የሚችል ችግር ነው። ምክንያቱም ክረምት ሲገባ በደንብ ነው የሚመቸው። የአካባቢው ጥበቃ ቢሮ ነው ይህንን ስራ በዋናነት የሚያስተባብረው። ስለዚህ ክረምቱ ከመግባቱ በፊት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ ሀሳብ (recommendation) እንሰጣለን ብለን እንገምታለን።

ናይል፡- አረሙ ጣና ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት ምን ይመስላል?

ዶ/ር ዋሴ፡- እንግዲህ እስካሁን ጣና ላይ ያየናቸው አንዳንድ ነገሮች በምርምር ብዙ የተደገፉ አይደሉም። ምርምሮቹን ገና አሁን በብዛት እየተሰሩ ነው ያለው። ግን በአጠቃላይ የአረሙን ባሕሪያት ከሌሎች ጋር ያደረሰውን ጉዳት ብንመለከተው ለምሳሌ በቪክቶሪያና በሌሎች ኬንያ ውስጥ ካሉ ብዙ ሐይቆች ላይ ከአረሙ ባሕሪ አንጻር ስንመለከተው አንድ ሐይቅን በማድረቅ የውሃውን ትነት ከ3 እስከ 5 እጥፍ ያሳድገዋል። በእንቦጭ አረም የተሸፈነን ውሃንና ንፁህ ውሃን ለክተን ብናየው ከ3 እስከ 5 ባለው ልዩነት ውሃውን የማትነንና የማድረቅ ባህሪ አለው። የአረሙ ትልቁ ችግር ውሃውን ማድረቅ ነው። በውሃው ላይ ችግር እንደሚያስከትል ምንም ጥርጥር

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

## “ለእኔ የሚገባኝ የግቢ ሕይወት ማለት ራሳችንን ሆነን ...

ከገጽ 8 የዞረ

የባሕል ልብስ ለብሰን እንድንገኝና የቀረቡትን ጥያቄዎች እንድንመልስ ተደረገ፡፡ ጥያቄዎች ለኔ ጥሩ ነበሩ፡፡ የቻልኩትን ያህል ለመመለስ ሞክሬ ስለነበር ዳኝነቱ ግልፅነት የሞላበት በመሆኑ አሸናፊ ሆኛለሁ፡፡

ናይል፡- እንደ አምባሳደርነትሽ ካንቺ ምን ይጠበቃል? አሁንስ ምን እየሰራሽ ነው?

ብዙአየሁ፡- በዋነኛነት ከእኔ የሚጠበቀው ለተማሪዎች አርአያ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ አሁን እየሰራሁ ያለሁት ከስርዓተ ፆታ ጽ/ቤት ጋር በመሆን ሴት ተማሪዎች በግቢ ውስጥ ለሚያጋጥማቸው ችግር ድጋፍ የሚያደርጉ ስልጠና የወሰዱ ተማሪዎች ሁሉም ሴት ተማሪዎች የመጡበትን ዓላማ አሳክተው እንዲመለሱ ታልሞ በፆታዊ ትንኮሳና በሌሎች ችግሮች ዙሪያ እየሰሩ ስለሆነ ከነሱ ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ክትትል በማድረግ የሴት ተማሪዎችን ችግር ለመፍታትና በራስ የመተማመን ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የተቻለኝን ሁሉ እየሰራሁ ነው፡፡

ናይል፡- ከትምህርትሽ ጐን ለጐን ያበረከትሻቸውን አስተዋፅኦዎች ስታከናውኚ የጊዜ አጠቃቀምሽ እንዴት ነበር?

ብዙአየሁ፡- ከተማሪዎች ሕብረት ውስጥም የሴቶች ጉዳይ ተጠሪ ስለሆንኩ አንዳንድ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመፍታት ከተማሪዎችና ከኮሌጁ አመራር አካላት ጋር በመወያየት የቻልኩትን ሁሉ እየሰራሁ እገኛለሁ፡፡ እነዚህንና ሌሎች ተግባራትን ሳከናውን የጊዜ አጠቃቀሜን ለማስተካከል የሚሰሩ ስራዎችን እንደ አስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል በማስያዝ ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ እየሰጠሁ እሰራለሁ፡፡

ናይል፡- ለስኬትሽ ሚስጥሩ ምንድን ነው?

ብዙአየሁ፡- ለስኬቴ ሚስጥሩ በዋነኛነት እግዚአብሄር ነው፡፡ በተጨማሪም የአስተዳደግ ሁኔታዬና ለነገሮች ትኩረት ሰጥቼ መስራት በመቻሌ ነው፡፡

ናይል፡- የሕይወት ፍልስፍናሽን እና ፍቅርን ከትምህርት ጋር በምን ዓይነት መልኩ ትገልጭዋለሽ?

ብዙአየሁ፡- የሕይወት ፍልስፍናዬ ለሁሉም ጊዜ አለው በሚለው አባባል ስለምመራ ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ መሰጠት አለበት የሚል ነው፡፡ ፍቅርና ትምህርት አንድ ላይ ይሄዳሉ ብዬ አላስብም፡፡ እንደኔ አስተያየት ግቢ ውስጥ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነገር ትምህርት ስለሆነ ውጤታማ ለመሆን ደግሞ ሌላ ትኩረት የሚሰብ ነገር አያስፈልግም፡፡ ምክንያቱም ፍቅር በባሕሪው ትኩረት የሚስብ ነገር ስለሆነ መሸሽ ያስፈልጋል ወይም አለማሰብና አለመጀመር ይቻላል እላለሁ፡፡

ናይል፡- የገቢ ምንጭሽ ከማን ነው? የምታገኚው ገንዘብስ በቂ ነው?

ብዙአየሁ፡- ገንዘብ የማገኘው ከቤተሰቦቸ ነው፡፡ የሰው ልጅ ፍላጐት ስለማይገታ በቂ ገንዘብ የሚባል በሰዎች ዘንድ ላይኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ራሳችንን መግዛት ከቻልንና በዋንኛነት ለሚያስፈልጉ ነገሮች ብቻ ወጭ ማድረግ ከተቻለ እርካታ ማግኘት ስለሚቻል እኔም በቂ እንዲሆን ማድረግ ችያለሁ፡፡

ናይል፡- ለሌሎች ተማሪዎች የምታስተላልፊው መልዕክት ምንድን ነው?

ብዙአየሁ፡- የማስተላልፈው መልዕክት በመጀመሪያ ልንሰራ ያቀድናቸውን ነገሮች ቅደም ተከተል ማስያዝ ለውጤታማነት እንደሚያበቃ፣ ለሕይወታችን ዋና የምንለውን ነገር ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ፣ ለራሳችን ጥሩ ግምት ሊኖረን እንደሚገባ፣ ስለራሳችን ሰፋ አድርገን ማሰብ አንጂ ወሰን ሊኖረን እንደማይገባ እንዲሁም በራስ የመተማመን ብቃታችንን ካዳበርን ዓላማችንን ማሳካት እንደምንችል እገልፃለሁ፡፡ ይህን ብዬ ለዚህ ሁሉ ስኬት ላበቃኝ ለእግዚአብሄር፣ ለቤተሰቦቼ፣ ለጓደኞቼ ለመምህሮቼ፣ ለተማርኩባቸው ት/ቤቶች ታላቅ አክብሮት ለምሰጠው ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ናይል፡- ስለነበረን ቆይታ ከልብ እናመሰግናለን!!

ብዙአየሁ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## ዩኒቨርሲቲው ለማሕበረሰብ ሬድዮ ጋዜጠኞች ስልጠና ሰጠ

በታድዬ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በአፋር ክልል የአርጐባ ማሕበረሰብ ልዩ ወረዳ የጋቺኒ ከተማ ለማሕበረሰብ ሬድዮ ጣቢያ ጋዜጠኞችና የቴክኒክ ባለሙያዎች መሰረታዊ የጋዜጠኝነት ሙያን ለአምስት ተከታታይ ቀናት ስልጠና ሰጠ፡፡ የስልጠናው ዋና ዓላማ ጋዜጠኞቹና የቴክኒክ ባለሙያዎቹ የማሕበረሰብ ሬድዮን ባሕርያትና ምንነት በመረዳት የማሕበረሰቡ ድምፅ በመሆን እንዲያገለግሉ ለማስቻል መሆኑን አሰልጣኙ ገልጸዋል፡፡ በጋዜጠኝነትና ተግባቦት መምህራን የተሰጠው ስልጠና በዜና ምንነት፣ ባሕርያት እና አፃፃፍ እንዲሁም የቃለ መጠይቅ እና የአርትኦት ስራ ሙያን በፅንሰ ሀሳብና በተግባር የተደገፈ ነው፡፡

የሬድዩ ጣቢያው በህብረተሰቡ የተቋቋመ በመሆኑ የጣቢያው በጀት በአብዛኛው የሚሸፍነው ከማሕበረሰቡ በሚገኝ መዋጮ ነው፡፡ ማሕበረሰቡ የቦርድና የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በመምረጥ ስራውን እያካሄደ ይገኛል፡፡ የጋቺኒ ከተማ ከአዲስ አበባ ከ700 ኪ.ሜ በላይ ከባሕር ዳር ... ኪ.ሜ ላይ የሚገኝ ሲሆን ማሕበረሰብ በዋናነት በግብርና፣ በሽማ ስራና ንግድ ይተዳደራል፡፡ በመጨረሻም አሰልጣኞቹ ከዚህ ቀደም የተሰጠውን ስልጠና ውጤት ለመገምገም ወደ ኮምቦልቻ፣ ሰቆጣና ዋግህምራ በመሄድ የስልጠናውን ውጤት ገምግመዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በአማራ ክልል ውስጥ በርካታ የማሕበረሰብ አገልግሎት በስፋት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ከሚሰጡት አገልግሎቶች መካከል አንዱ ስልጠናዎችን ማዘጋጀትና መስጠት ነው፡፡ ለመምህራንና ርዕሰ መምህራን የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ እንዲሁም ለሌሎች ባለሙያዎች የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን እየሰጠ ይገኛል፡፡ በመሰረታዊ የጋዜጠኝነት ስልጠና በቅረቡ በኮምቦልቻና ሰቆጣ በሚገኙ የማሕበረሰብ ሬድዮ ጣቢያ ላይ ለሚሰሩ ጋዜጠኞችና የቴክኒክ ባለሙያዎች መስጠቱ ይታወሳል፡፡

### ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ጊዜ እና ጊዜአችን

በነብዩ ንጉሴ

2ኛ ዓመት ጋዜጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ትምህርት ክፍል

ስለ ጊዜ ሁላችንም የተለያየ ግንዛቤ፣ አመለካከት እና እሳቤ አለን፡፡ ሁሉም ነገር የሚከወነውም በጊዜ እንደሆነም እናውቃለን፡፡ የጊዜን ተፈላጊነት ብሎም ውድነት ስንናገር እውቀቱ ኖሮን፤ ለጊዜ ተቆርቋሪ ሆነንም ነው፡፡ ግን ግን.... እኛው ራሳችን ለስራ ሳይሆን ለጨዋታና ለቀልዳ ቀልድ የምናጠፋው ጊዜ እጅጉን ሰፊ ስለመሆኑስ ተገንዝበን ይሆን? ...

ጠቢቡ ሰለሞን «ለሁሉም ጊዜ አለው» ማለቱ በእኛነታችን ውስጥ የሰረፀ ስለመሆኑም በግሌ ጥርጥር የለኝም አይኖረኝም፡፡ ለዚህ ደግሞ አንድና ሁለት የለውም፡፡ ለመኝታም ጊዜ አለው፤ ለጨዋታም ሆነ ለመዝናናት ጊዜ አለው፤ የታመመ ለመጠየቅም ጊዜ አለው፤ የታሰረ ለመጉብኘትም ጊዜ አለው፤ ለመብላትም ሆነ ለመጠጣትም ቢሆን ጊዜ እንዳለው እኔም እናንተም እንናገራለን፡፡ ይሁንና እኔን ግርም የሚለኝ ስለ ጊዜ ጠቀሜታ በሚገባ የምናውቅና የምንናገር ብንሆንም በአልባሌ ነገሮች፣ በዋዛ ፈዛዛ ስናጠፋው ልብ ያለማለታችን እንዲያም ሲል ያለማፈራችን ነው፡፡ ይህ እውነታ አይገርምም ትላላችሁ?.....

እንዲያው ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን ሀዘንም ሆነ ችግር የደረሰበት ወዳጃችንን ወይም ደግሞ በማንም በምንም ምክንያት ሊጠየቅ የሚገባውን ጓደኞችንን ስንጠይቅና በሀዘኑም ሆነ በችግሩ ጊዜ ሳንደርስ ቀርተን በድንገት ስንገናኝ «ሳይመቸኝ ቀርቶ» ...... «ጊዜ አጥቼ»..... በማለት ጊዜን ማማካኛ የምናደርግ?.... እእ.... ተውት... ልብ ለልብ ስለምንተዋወቅ ጥያቄ ጠየቅኩ እንጂ መልስ አልፈለኩም፡፡

ጊዜ የሚያጥረው ሰው ለስራ ትኩረት የሚሰጥ እንጂ የባጡን የቆጡን ሲያወራ የሚውል አይደለም፡፡ እናስ?.... እኛስ ታዲያ?... እኔንና እናንተን ማለቴ ነው...... ጊዜ ያጥረናል አይደል?!

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ብዙዎችን ሥራ በዝቶብን መተንፈስ ሁሉ እንደተሳነን ስንናገር መደመጣችን ነው፡፡ ይህም የሚያስተዛዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ይህን ስል ታዲያ በየትኛውም የስራ መስክ ስራ የሚበዛበት ሰው እንደሚኖር አለመዘንጋቴን እወቁልኝ፡፡ ይሁንና ጊዜ እያለን የዛሬን ስራ ሳናሳድር ዛሬውኑ ከውነን ለነገው ሥራችን የምንዘጋጅ አለመኖራችንን እኔ ብቻ ሳልሆን እናንተም የምትመሰክሩ ይመስለኛል፡፡

አሁን ልንሰራው ልንከውነው የሚገባንን ስራ ተወት በማድረግ የሻይ ሰዓት ደረሰም አልደረሰም ብለን ከስራ ገበታችን ላይ ተነስተን ወጥተን በዚያው ቅልጥ የምንል ብዙዎች ነን፡፡ የሻይ ሰዓታችን 15 ደቂቃ ወይም ደግሞ 20 ደቂቃ ሆኖ ሳለ ብዙ ሰዓት በመውሰዳችን ምሳ ሰዓት ይደርሳል፡፡ ከዚያም ቀጣይ የምናደርገው ስራ ደግሞ ምሳ መብላት ነው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን ጊዜውን የምንገፋ በቁጥር ጥቂት የምንባል አይደለንም፣ ኧረ እንደውም በርከት እንላለን፡፡...... እና ታዲያ ይህን እያደረግን «ስራ በዛ» ማለቱን ምን አመጣው?! የምን ቅጥፈት ነው ጎበዝ!.... በዚህ አጋጣሚ ዝም ብሎ በከንቱ የባከነ ጊዜ ስለመኖሩ አስተውለን ይሆን? በጊዜ ላይ ቁማር እየተጫወትን እንደሆነስ ይጠፋን ይሆን?..... ያም ሆነ ይህ ግን ጊዜን በሚገባ ማስተዋል፣ መረዳትና ማወቅ አለብን እላለሁ፡፡ ይህ ካልሆነ በእኛ ምክንያት የሚፈጠሩ ለውጦችን እናዘገያለን፣ ውጤታማም አንሆንም፡፡

**አሁን ልንሰራው ልንከውነው የሚገባንን ስራ ተወት በማድረግ የሻይ ሰዓት ደረሰም አልደረሰም ብለን ከስራ ገበታችን ላይ ተነስተን ወጥተን በዚያው ቅልጥ የምንል ብዙዎች ነን፡፡**

ጊዜያችን የምናባክንበት ሌላው አልባሌ ስራችንን ደግሞ እንመልከት፡፡ የሰው ሥም እያነሳን ስንጥል፤ በሀሜት ጥይት ስንቆላውና ስንጠባብሰው፤ በአሉቧልታ ቦንብ ስናፈነዳው፤ ያልሆነውን ሆነ ያልተባለውን ተባለ እያልን ወሬያችንን ስንሰልቅ የምንገኘው በዚሁ ጊዜያችን አይደለምን?.... ነውና፡፡ እናስ ታዲያ መለስ ብለን ልንሰራበት በሚገባን ጊዜ ስናወራበት ቆይተን «አጠረን» አለያም «አጣን» ስንል ለትዝብት አይዳርገንም?..... ኧረ ይዳርገናል ጎበዝ! ብቻ.... 'ጊዜ' ከምንም በላይ ውድና ተፈላጊ ነውና ለቁም ነገር ብናውለው መልካምነቱ ይጐላል፡፡ ዛሬ'ኮ ጊዜ ሁሉንም ነው፡፡ ተዓምር ተሰራ ቢባል በጊዜ ነው፡፡ አዲስ ግኝት ተገኘ ተፈበረከ ቢባል በጊዜ ነው፡፡ አዲስ ሳይንሳዊ ምርምር ይፋ ሆነ ቢባል በጊዜ ነው፡፡ የኑሮ መሻሻል፣ የሕይወት ጣፋጭ መሆን ሁሉ የሚከናወነው ያው በጊዜ ነው፡፡ እናም.... ጊዜን ስንሰራበት እንጂ በከንቱ ስናባክነው ስናወራበት ባንገኝ መልካም ነው ባይ ነኝ፡፡

ምንም ሳንሰራበት በተራ ነገር ሲያልፈን'ወይ ጊዜ' ብለን ማዘኑንና መቆጨቱን እንተው፡፡ ለማስመሰል «busy» ነኝ ማለቱ ይብቃን፡፡ ጊዜን እንስራበት፤ እንለወጥበትም፡፡

ሁሌም በጊዜያችን እንስራበት፡፡ የግል ኑሮአችንንም ሆነ የሀገራችን የድህነት ቀንበር መስበር የምንችለው ጊዜን በአግባቡ ስንጠቀምበትና ስንሰራበት እንጂ ስናወራበት እንዳልሆነ ማንም ሳይነግረን የምናውቅ ይመስለኛል፡፡

ለማንኛውም ስለጊዜ ማለት ያለብኝን በማለት መልዕክቴን ያስተላለፍኩ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ በላይ ብቀጥል ውድ ጊዜያችሁን መስረቅ ነውና የሚሆንብኝ ላጠናቅቅ ወድጃለሁ፡፡ ሀሳቤን ሰብሰብ አድርጌ አስሬ ስደመድም ግን ተማሪዎች በማንበብ፣ በማጥናት፣ በመማር፣ በመመራመር ና እውቀት በመቅሰም ጊዜያችንን እንጠቀምበት፡፡ መምህራንም በበቂ ሁኔታ በመዘጋጀት፣ በትምህርት ክፍል ጊዜ በሰዓቱ በመገኘት ለማስተማርና ተማሪዎችን እውቀት ለማስጨበጥ ጊዜያችሁን ተጠቀሙበት፡፡ ሁላችንም ጊዜያችንን በእቅድ እንምራው፣ እንስራበት እንጠቀምባት እላለሁ፡፡ ደህና ሁኑ!

# ካስኬፕ ፕሮጀክት ...

ከገጽ 4 የዞረ

የሆላንድ አምባሳደር የተቋቋመ ሲሆን በዋግነር (Wagneniger University) ድጋፍ ይደረግለታል፡፡ ዶ/ር ይኸነዉ የፕሮጀክቱ ዋና አላማ የግብርና ችግሮችን መለየትና መቀመር፣ መልካም ተሞክሮዎችን ለማስፋፋት የሚያግዙ እውቀቶችን ማመንጨት እንዲሁም የሰርቶ ማሳያ ስራዎችን ማከናወን መሆኑን ገልጸው ለአስራ ሶስት የግብርና ሰራተኞች የ2ኛ ዲግሪ እንዲሁም ለአንድ መምህር የ3ኛ ዲግሪ የትምህርት ወጭ በመሸፈን የአቅም ግንባታ ስራ በሰፊው እየሰራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ግብርና የአገራችን የጀርባ አጥንት መሆኑን በመረዳት ፕሮጀክቱ ምርት እያሳደገና መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን ለማስፋፋት ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው ብለዋል፡፡

ዶ/ር ይኸነዉ አክለውም ፕሮጀክቱ የአርሶ አደሩን ችግሮች በምርምር በመለየት ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚገኙትን ቴክኖሎጂዎች ከአርሶ አደሩ ጋር በማስተዋወቅ ችግሮችን መፍታት እንደቻለ ገልጸዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ከዚህ ቀደም በለጠ የሚባል የድንች ዘር ለአርሶ አደሩ በማከፋፈል አርሶ አደሩ በሄክታር ያገኝ የነበረውን ምርት በእጥፍ በማሳደግ ህይወታቸውን እንደተቀየረ በተለይ የምግብ ገብስ ምርጥ ዘር ከዚህ ቀደም በሄክታር ይገኝ የነበረውን 14 ኩንታል ምርት ወደ 29 ኩንታል በማሳደግ ከፍተኛ ምርት አርሶ አደሩ እንዲያገኝ እገዛ ተደርጓል ብለዋል፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ የፕሮጀክቱ የእንስሳት ባለሙያ አቶ የኔሰው አበበ እንደስረዱት በአማራ ክልል ከፍተኛ ቁጥር ያለው የእንስሳት ሀብት ቢኖርም የሚገኘው ምርት ግን አናሳ መሆኑን ገልፀው በመኖ እጥረትና ጥራት ማነስ ምክንያት የእንስሳት ምርት በተገቢው መልኩ ስኬታማ ማድረግ ባለመቻሉ ይህን ለመቅረፍ አርሶ አደሩ የሮደስ ሳርን በማምረት ምርታማነትን መጨመር እንደሚችል በጥናታቸው ገልጸዋል፡፡ አቶ የኔሰው አክለውም የሮደስ ሳር ከ3-17 በመቶ የፕሮቲን ይዘት ያለውና የመርዛማነት ባሕርይ ስለሌለው መሬትን ከመሸርሸር ይከላከላል ብለዋል፡፡ ፕሮጀክቱ የሮደስ ሳር ለእንስሳት መኖ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው በጥናትና ምርምር በመረጋገጡ በፕሮጀክቱ የታቀፉ አርሶ አደሮች ጓሮ የሮደስ ሳር እያበቀለ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ አዳዲስ ዝርያዎች ሲመጡ አርሶ አደሩ እንዲያውቃቸው እያደረግን ነው ብለዋል፡፡

በመድረኩ የወረዳ አስተዳዳሪዎች፣ አርሶ አደሮች፣ የግብርና ባለሙያዎች የተገኙ ሲሆን አርሶ አደሮች በፕሮጀክቱ በሚደረግላቸው ድጋፍ ምርታቸው ማደጉንና ኑሯቸው መቀየሩን ተናግረዋል፡፡ ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ 6 ዩኒቨርሲቲዎች ማለትም በባሕር ዳር፣ በሀዋሳ፣ በአዲስ አበባ፣ ጅማ፣ መቀሌና ሀሮማያ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲው ፕሮጀክት በደራ፣ በሜጫ፣ ደቡብ አቸፈር ጃቢ ጠህናን እና ቡሬ ወረዳዎች ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡

## የሳይንስ ኮሌጅ ...

ከገጽ 4 የዞረ

ለማድረግ ዩኒቨርሲቲዎች ጠንክረው መስራት እንዳለባቸው ገልጸው በቅድመ ሳይንሳዊ ታሪካችን ላይ ብዙ ምርምር በማድረግ አባቶቻችን አክሱምን እንዴት አቆሙት? ላሊበላን እንዴት ሠሩት? የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ሳይንሳዊ እሳቤዎችን ማስፋት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡ ሳይንስን በራሳችን ቋንቋ በመጠቀም ኢትዮጵያዊ ሳይንሳዊ እሳቤ እንዲኖር የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ተመራማሪዎች እርስበርስ እንዲወያዩበትና የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲያስቀምጡት አሳስበዋል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከመማር ማስተማር በተጨማሪ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በህክምና፣ በውሃና በሌሎችም ዘርፎች ምርምር እያካሄደ እንደሚገኝና ለማህበረሰብ አገልግሎትም ትኩረት በመስጠት እየሠራ እንደሚገኝ በዩኒቨርሲቲው አካባቢ ያለ/ች ተመራማሪ የምርምር ሃሳብ ይዞ ከመጣ/ች ዩኒቨርሲቲው ለመርዳት ፍላጎት እንዳለው ዶ/ር ባይሌ አሳውቀዋል፡፡

በጉባኤው ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባዮሎጂ ትምህርት ክፍል መምህር ፕሮፌሰር አፈወርቅ በቀለ ሳይንስ ለኑሯችንና ለአገር እድገት በጣም አስፈላጊ እንደሆነና ሳይንስን ወደ ተግባር በመቀየር የማህበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ መቀየር ከተማረው ማህበረሰብ የሚጠበቅ ጉዳይ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጀምሮ የሳይንስ ዕውቀት ላይ ግንዛቤ መፍጠር የዩኒቨርሲቲዎች ግዴታ እንደሆነና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ኮሌጅ እንዲሁም ዩኒቨርስቲው የሳይንስን ግንዛቤ ለመፍጠር በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ እየሠሩ ያለው ሥራ ሊበረታታ የሚገባ ጉዳይ እንደሆነና ወደፊትም ከዚህ የበለጠ ጠንክሮ እንደሚሰራ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል፡፡

## ተቋሙ አለም አቀፍ ...

ከገጽ 5 የዞረ

ጊዜ እየተካሄደ ያለው ጉባኤ አላማን ሲገልጹ ለአገር የሚጠቅሙ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማፈላለግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ጉባዔው የተቋሙ መምህራን ስራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ተነሳሽነት የሚፈጥርላቸው መሆኑን ገልጸው አለም አቀፍ ጉባዔ እንደመሆኑ መጠን የውጭ ሀገር ተመራማሪዎችን በስፋት በማሳተፍ ልምዳቸውን የሚያጋሩበት እንዲሆን ጠንክረን እንሰራለን ብለዋል፡፡

የተቋሙ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ዶ/ር ንጉስ ጋብየ በበኩላቸው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምእተ ዓመቱን ግብ ለማሳካት በምርምር፣ በሰው ሀይል አስተዳደር እንዲሁም በቴክኖሎጂ የ2ኛና የ3ኛ ዲግሪዎችን በማስፋፋት ላይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለጉባዔው ተሳታፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ዩኒቨርሲቲው የመንግስትን አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ልዩ ትኩረት በመስጠትና ከፍተኛ የምርምር በጀት በመመደብ እየሰራ መሆኑን ገልፀው ተማሪዎች በሳይንስና ቴክኖሎጂ ለውጥ በማምጣት በአለም አቀፍና በሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ተቀጥረው እንዲሁም የራሳቸውን ኩባንያዎች ከፍተው ራሳቸውንና ሕዝባቸውን እንዲጠቅሙ ጠንክረን እየሰራን ነው ብለዋል፡፡ ዶ/ር ባይሌ “Radio Science Research at Washera Geo-space and Radar science Laboratory” የሚል ጥናታዊ ግኝታቸውን ለተሳታፊዎች አቅርበዋል፡፡

ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና በግል የመጡ ተመራማሪዎችና የውጭ ሀገር ምሁራን በጉባዔው የተሳተፉ ሲሆን በ Communication System Engineering, Construction materials & Management, Environmental Science Energy እና ተያያዥነት ባላቸው ርዕሶች ላይ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል፡፡ በጉባዔው ላይ የስእል እና የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ የቀረበ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ተመራቂ ተማሪዎች የሳይንስና ቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራዎቻቸውን አቅርበዋል፡፡

## የአማርኛ ቋንቋና የባሕል ዘርፎች ...

ከገጽ 4 የዞረ

መቀጠል እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ዓ.ም አፍሪካ ውስጥ ካሉ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን እየሰራ እንደሚገኝና ለዚህም ራዕይ ስኬት በሁሉም የትምህርት መስኮች ሣምንታዊ የምርምር ሴሚናርና አመታዊ አውደ ጥናቶች በማካሄድ ላይ እንደሚገኝ የተናገሩት የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ናቸው፡፡ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲም በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማሕበረሰብ አገልግሎት የማሕበረሰቡን ችግሮች ሊቀርፉ የሚችሉ ጥናቶችን እያካሄደ መሆኑን ጠቁመው በተለይ የአማርኛና የፎክሎር ትምህርት ክፍሎች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ እያካሄዱት ያሉት የተለያዩ አውደ ጥናቶች ለተመራማሪዎች፣ ለጀማሪ መምህራን፣ ለድህረ-ምረቃ ተማሪዎች ትልቅ ግብአት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

3ኛው አገር አቀፍ አውደ ጥናት በተለያዩ ጥናቶች ላይ ትኩረት የሰጠ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሁለተኛ ሳይክል ሙያዊ ቃላትን በማበልፀግ፣ መደበኛ ማድረግና በመተግበር ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች፣ የአማርኛን የአፃፃፍ ስርዓት ማሻሻል፣ መሰንቆ አካባቢያዊ ትርጉሙና ተግባር፣ የአማርኛ ሥነ-ጽሁፍ ሂስ ከወርሃ ጽንስ እስከ ወርሃ ዳዔ፣ የባሕል ግጭት በአደፍርስ፣ በዘጌ ባህረ ገብ መሬት ላይ በሚገኙ ገዳማት ውስጥ የተሳሉ ጥንታዊ የግድግዳ ስዕሎች ፋይዳ እና ሌሎቹም ጥናታዊ ጽሁፎች ለሁለት ተከታታይ ቀናት ቀርበዋል፡፡

ፋኩልቲው በየዓመቱ ለሚያካሂደው አውደ ጥናት ግብአት ይሆን ዘንድ ጠንካራና ደካማ ጐኖችን ለመለየት ያግዝ ዘንድ ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት አድርጓል፡፡ ጥናታዊ ጽሁፎቹ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያግዙና ለፖሊሲ አውጪዎችም ግብአት እንደሚሆኑ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ በደቡብ አፍሪካ፣ በየመን እና በሊቢያ በኢትዮጵያዊያን ላይ ለተፈፀመው ግድያ የሕሊና ፀሎት በማድረግ አውደ ጥናቱ ተጠናቋል፡፡

## ለኢንዱስትሪ ዕድገት ከፍተኛ የትምህርት ...

ከገጽ 5 የዞረ

ከሀገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ በሚስማማ መልኩ በመተርጐም የሀገሪቱን የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ወደ አንድ ምዕራፍ ከፍ ማድረግ እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የጨርቃ ጨርቅና ፋሽን ዲዛይን ቴክኖሎጂ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አዲሱ ፈረደ በበኩላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመራማሪዎች፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች እና የጥሬ እቃ አምራቾች በጋራ በመስራት በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርት እድገት ላይ ያሉትን ተግዳሮቶች በመለየት በጥናት ላይ የተመሰረተ ዘላቂ መፍተሄ ማስቀመጥ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ አቶ አዲሱ አክለው እንደተናገሩት ተቋማቸው በዚህ ዘርፍ ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ክፍተት ከመሙላት በተጨማሪ በምርምር፣ ማህበረሰብ በማማከር እና ለኢንዱስትሪው የሚውሉ ጥሬ እቃዎች ጥራታቸው የተረጋገጠ እንዲሆን በቤተ ሙከራ በማረጋገጥ ለፋብሪካዎች በግብአትነት እንዲጠቀሙባቸው በማድረግ ዙሪያ ሰፊ ስራ እየሰሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

የጉባዔው አላማ ጥናታዊ ፅሁፎች እንደ መነሻ ሐሳብ በመውሰድ በሐገሪቱ ውስጥ በምርምር የታገዘ ለዘርፉ በግብአትነት የሚያገለግል ጥሬ እቃ በማምረት ኢንዱስትሪውን በአለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊ የሆነ ምርት ማምረት የሚያስችል አቅም መፍጠር እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በጉባዔው ላይ ከአገርና ከውጭ ውስጥ በዘርፉ ሰፊ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን ተጋብዘው 15 ጥናታዊ ፅሁፎች አቅርበው በተሳታፊዎች ውይይት ተደርጐባቸዋል፡፡ የክልልና የፌዴራል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የውጭና የሀገር ውስጥ ተመራማሪዎች፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሐብቶች፣ መምህራንና ተማሪዎች በጉባዔው ላይ የተሳተፉ ሲሆን በተማሪዎች የተሰሩ የፈጠራ ስራዎች አውደ ርዕይ እና የፋሽን ሾው ትዕይንት በማቅረብ ጉባዔው ተጠናቋል፡፡

## የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ

ከገጽ 4 የዞረ

በምስረታው ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ዲኤታ አቶ ሙሉጌታ ሰይድ በበኩላቸው ተቋሙ በዘርፉ ተመራማሪዎችን ለማፍራት በትጋት መስራት እንዳለበት ጠቁመው ቋንቋዎች ላይ የሚሰሩ ምርምሮችን በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሁሉም ቋንቋዎች ላይ ማድረግ የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተልዕኮው በመሆኑ ተቋሙን መስሪያ ቤታቸው እንደሚያግዝ ገልጸዋል፡፡

በጉባዔው ላይ የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን ከነዚህ መካከል ቋንቋ እንዴት ይበለፅጋል በፕሮፌሰር ባዬ ይማም፣ በቋንቋ እቀዳ የአንዳንድ ሀገራት ተሞክሮ በዶ/ር ታየ አሰፋ፣ አማረኛ ቋንቋ ከየት ወደ የት? (ስነ ልሳናዊ ዳሰሳ ጥናት) በዶ/ር ዘላለም ልየው እንዲሁም በትግበራ ወቅት በአማርኛ ቋንቋ ላይ የሚታዩ ግድፈቶችንና መፍትሄያቸው በዲያቆን ዳንኤል ክብረት ይገኙበታል፡፡

የተቋሙን ምስረታ አስመልክቶ አጠቃላይ ውይይት በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው አማካኝነት የተደረገ ሲሆን የተቋሙ ዳይሬክተር ዶ/ር ሂሩት ካሳው የተቋሙን አላማና ተግባር አስተዋውቀዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራውና የተቋሙ ዳይሬክተር ዶ/ር ሂሩት ካሳው ከቀናት በፊት የተቋሙን ምስረታ አስመልክቶ ከተለያዩ የብዙሀን መገናኛ ለመጡ ጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠታቸው ይታወሳል፡፡

በምስረታ በአሉ ላይ ደራሲዎች፣ አርቲስቶች፣ የስነፅሁፍ ባለሙያዎች፣ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማሕበር ተወካዮች፣ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ መምህራን እንዲሁም ከሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመጡ ሀላፊዎች የተሳተፉ ሲሆን የተቋሙን ምስረታ አስመልክቶ ገንቢ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የአማርኛ ቋንቋን ለማሳደግ እስከ 3ኛ ዲግሪ ድረስ ትምህርት እየሰጠ ይገኛል፡፡

## ሀገር አቀፍ አውደ ...

ከገጽ 4 የዞረ

እንዲሰሩ ታቅዶ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የሕግ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ዶ/ር ሚዛን አባተ የአውደ ጥናቱን አላማ መልካም አስተዳደርን በማስፈንና ዘላቂ ልማትን በማስፋፋት ሀገሪቱን ከፍተኛ ደረጃ ላይ ካሉ ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ የተሰሩ ምርምርና ጥናቶችን ለማህበረሰቡና ለአጋር አካላት ማድረስ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

መልካም አስተዳደር ለዘላቂ ልማት ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በተመለከተ የተለያዩ ፅሁፎች ቀርበው ከተሳታፊዎች ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን ለፖሊሲ አውጭዎች ግብአት የተገኘበት መሆኑን ተሳታፊዎች ተናግረዋል፡፡ በአውደ ጥናቱ ላይ የቀረቡት ፅሁፎች ትምህርት ቤቱ በሚያዘጋጀው መፅሔት ላይ ታትመው ለዩኒቨርሲቲዎች፣ ለመንግስት ተቋማትና ለአጋር አካላት እንደሚሰራጩ ታውቋል፡፡

በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት አቶ ዳንኤል ተሰማ ከጥናት አቅራቢዎች አንዱ ሲሆኑ ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞ በሀገራችን የተለያዩ ችግሮች መኖራቸውን ገልጸው ችግሮቹን በመለየትና የመፍትሄ ሃሳብ በማምጣት በፖለቲካና በኢኮኖሚ ረገድ ሀገሪቱን ወደ ተሻለ አቅጣጫ እንድትጓዝ ከምሁራን ብዙ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡ ምሁራን ከማስተማር ባለፈ ጥናታዊ ጽሑፎችን በማቅረብ የሚታዩ ክፍተቶችን በማጉላት መንግስትና አጋር አካላት ምርምሮችን ወደ ተግባር በመለወጥ ሃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

# ያልተከደነው ትዳር

## አጭር ልብወለድ

በፍሬዘር ታሪኩ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል ተማሪ

ኤፍሬም የቢሮ ወንበሩ ላይ እግሩን ወደ ስር አጣምሮ ዘርግቷል፡፡ በተከሻው ወደ ኋላ ደገፍ በማለት እናቱ እንደሞተበት ሀዘንተኛ አንጀቱን ጭንቅላቱ ላይ ቆልፎታል፡፡ ፊቱ ግን የቅቤ ማንኪያ ይመስላል ወዝቶ ደስ የሚል የፍቅር ፈገግታ በባዶ ቢሮ ውስጥ ይረጫል፡፡ ከዚህ ከማይለቀው የሀሳብ ዋሻ ውስጥ ድንገት ወጣና በፊት ለፊቱ የሚገኘውን የፎቶ ፍሬም ለማንሳት ሲል እግሮቹን ሰብሰብ አድርጐ እጆቹን ከአናቱ ላይ አውርዶ ዘረጋቸው፡፡ እጆቹን ሲዘረጋ ግን መጫወቻ እንዳየ ህፃን ልጅ በፈገግታ ነበር ለማንሳት የተንሰፈሰፈው፡፡ በቅርቡ የወለደው ሕፃን ልጁ እና የሚስቱ ነበር ፎቶው፡፡ በፍቅር እይታ አይኖቹን እያስለመለመ አየና ሳመው፡፡ «የደስታና የሰላም ምንጭ ነሽ ነፂ» አለና አስቀመጠው፡፡

ኤፍሬም የእድሜውን እሩብ ያሕል ሲመኛትና ሲንገበገብላት የነበረችውን ነፃነትን ዛሬ ላይ ተሳክቶለት አግብቷታል፡፡ ጓደኛው ተሾመና ኤፍሬም በፍርድ ቤት ውስጥ አብረው በሚሰሩበት ጊዜ ነፃነትም አብራቸው ትሰራ ነበር፡፡ ኤፍሬም ከተሾመ ጋር ከፍተኛ ፉክክር አድርጐ ነው ያገባት፡፡ ከዛ ሁሉ ትግል በኋላ እንዳገባት አብረው ለየግላቸው የጥብቅና ስራ በመስራት ከሁለት አመት በላይ አስቆጥረዋል፡፡ ሁሌም በትዳር አለም ውስጥ በጣም ደስተኛ እኔ ብቻ ነኝ ብሎ ያስባል፡፡ የትግሉ አሸናፊ ነኝ ብሎ ስለሚያስብም እራሱን የጀግና ያህል ነው የሚቆጥረው፡፡

የእጁን ሰዓት አየና ሰዓት እንደሄደ ባወቀ ጊዜ የሱፉን ኮት ከሰቀለበት በማንሳት ቢሮውን ቆልፎ ወጣ፡፡ ከነበረበት ፎቅ ደረጃ መውረድ ሳይጀምር ቆሞ አሰበ፡፡ ዛሬ መኪናውን ጋራዥ እንዳስገባ አወቀና ተሰላቸ፡፡ ኮንትራት ገጃጅ ይዞ ለመሄድ አስቦ በየቦታው ማስቆሙን ሲያስብ ሀሳቡን ተወው፡፡ ከዛም ከሶስተኛ ፎቅ ደረጃውን መውረድ ጀመረ፡፡ ህንፃውን ጨርሶ እንደወጣ ግራውን ይዞ ትንሽ እንደሄደ ዘወትር እንደሚያደርገው ሙዝና ብርቱካን ገዛና ወደፊት እየገሰገሰ በኵራት የተነጣለለውንና የከተማውን ውበት ያጐለበተው ብሎም ከፍቅር ሀይቅ ጀምሮ እይታ ውስጥ የሚገባውን የቅዱስ ገብርኤልን ቤተክርስቲያንን ከበሩ ላይ ተሳለመ፡፡ በእግሩ የቤተ ክርስቲያኑን ቀኝ ይዞ ተራመዶ ትንሽ እንደሄደ ወደ ግራ ታጠፈ፡፡ ሰፈሩ ከቤተ ክርስቲያን ጀርባ ነው፡፡ በተለምዶ ስሙ ኢዩቴ ይባላል፡፡

ልቡ ነፃነትንና በቅርቡ የወለደውን ልጁን ለማየት ተጨንቋል፡፡ ከወጣ ይፈራል፡፡ ከገባም ይባባል፡፡ ለሚስቱም ሆነ ለልጁ ትልቅ ፍቅር ስላለው ከቤት ሲወጣ ደስተኛ አይደለም፡፡ ከአልጋው ጠዋት የግዱ ሲነሳ እንኳ መንጋቱን ይረግማል፡፡ ያፈቀረው በልቡ ብቻ ሳይሆን በነፍሱም ጭምር ነው፡፡ ሲመሽ ፈጣሪን ያመሰግናል፡፡ ሲነጋ ደግሞ ፈጣሪን ያማርራል፡፡

መሽቷል፡፡ ከመሸቱ አንድ ሰዓት ከሃያ ይላል፡፡ ይህ ሰዓት ባሏ ብርቱካንና ሙዝ ይዞ ስለሚመጣ በሳህን ላይ ቢላዋ ዘርግታ በሶፋው መሐል ላይ በሚገኘው ጠረንጴዛ ላይ አስቀመጠች፡፡ ጠረጴዛው መሀል ላይ አበባ የተቀመጠበት ተለቅ ያለ ጠርሙስ አለ፡፡ ወደ ሶፋው መለስ ብላ ያስተኛችውን ሕፃን ስታነሳ በር ተንኳኳ "ይግቡ" አለች መልከ መልካሟ ነፃነት፡፡ ስትናገር በጣም የተረጋጋች ናት፡፡ የተበሳጨን እንኳ በድምጿ ታስክናለች፡፡

በሩ ተገፍቶ የገባውን ሰው ስታየው ፊቷ ጠቋቆረ፡፡ በገባው ሰው ደስተኛ አለመሆኗን ሳትናገር በፊቷ ገለፀች፡፡

> ልቡ ነፃነትንና በቅርቡ የወለደውን ልጁን ለማየት ተጨንቋል፡፡ ከወጣ ይፈራል፡፡ ከገባም ይባባል፡፡ ለሚስቱም ሆነ ለልጁ ትልቅ ፍቅር ስላለው ከቤት ሲወጣ ደስተኛ አይደለም፡፡ ከአልጋው ጠዋት የግዱ ሲነሳ እንኳ መንጋትን ይረግማል፡፡ ያፈቀረው በልቡ ብቻ ሳይሆን በነፍሱም ጭምር ነው፡፡

«ደህና አመሸሽ ነፂ» አለ፡፡ ተሾመ ካገባችም በኋላ እቤቷ ይመጣል፡፡ ነፃነት ግን እቤቷ ሲመላለስ ምን ፈልጐ እንደሆነ ስለምታውቅ ሁሌ ትረበሻለች፡፡ ወደ ላይ እንደሚለው ሰው እሱ ሲመጣ ያንገሸግሻታል፡፡ ነፃነት እሱ መሆኑን ስታውቅ "እግዚአብሄር ይመስገን" ብላ ልጇን ልብስ ማልበስ ጀመረች፡፡ እሱ ወደ ቤቱ ዘልቆ በመግባት እጁን ዘረጋላት፡፡ እሷም ዘረጋችለት፡፡ ከእጅ ዝርጋታው በኋላ ወደ ታች ዝቅ በማለት ሊስማት ተንደረደረ፡፡ መሳሟን ስላልወደደች ፊቷን አዞረች፡፡ በሁኔታው የተናደደው ተሾመ «ምን ሆነሻል?» አላት፡፡

"ምንም"

"ታዲያ ለምንድነው የማትስሚኝ?"

"እኔና አንተን ለመሳሳም የሚጋብዘን ቀረቤታ የለንም ብዬ ከዚህ ቀደም የነገርኩ መሰለኝ ለምን ግን አተወኝም?"

"አትተወኝም?" የምፀት ሳቅ ሳቀባት፡፡ "አትተወኝም ማለት ምን ማለት ነው? እንዴት ነው ሰው የራሱን ንብረት የሚተወው?"

ደምስሮቿ መነበብ ጀመሩ፡፡ አይኖቿ ደመኛውን እንዳገኘ ገዳይ ተጉረጠረጠ፡፡ ከተቀመጠችበት ነጥራ በመነሳት ፊቱን በጥፍሯ የታረሰ መሬት ብታደርገው ደስ ባላት ነበር፡፡ ዳሩ ግን ሰጋች፡፡ «አንተ ሰውዬ ለምንድን ነው በትዳሬ ላይ እየመጣ ድንገተኛ ማዕበል የምትሆነው? ቆይ እኔ የምለው ገዝተኸኛል እንዴ ንብረት ንብረት የምትለው፡፡»

ኮቱን አወለቀና ከረቫቱን በማላላት ሶፋው ላይ ተቀመጠ፡፡ ቀኝ እግሩን በግራ እግሩ ላይ ሰቅሎ በመገረምም አያት፡፡ ነፃነትም በመለማመጥ ስሜት «እባክህ አሁን ልጄ ይተኛበት አታስጨኸኝ» አለችው፡፡

በዚህ ሰዓት ኤፍሬም ሚስቱንና ልጁን ለማየት እንደጓጓ ወደ ግቢ ገባ፡፡ ከዚህ በፊትም ነፃነትና ተሾመ በዚህ ጉዳይ ቢጨቃጨቁም ኤፍሬም ሲመጣ የመኪና ድምፅ ስለሚሰሙ ጭቅጭቁን ያቆሙ ነበር፡፡ ዛሬ ግን የመኪና ድምፅ የለም፡፡ የኮቴ ድምፅ ደግሞ መስማት አልቻሉም፡፡ ኤፍሬም ግን ከቤቱ የሚወጣ የጭቅጭቅ ድምፅ ሰማ፡፡ ቀስ ብሎ ተራመደና በመስኮት ሁኔታውን ይከታተል ጀመር፡፡

ተሾመ ከተቀመጠበት ተነሳና «አንቺ ሴትዮ ይህን ህፃን ልጄ አትበይ! የእኔም ልጅ እንደሆነ ታውቂያለሽ፡፡» ነፃነት ከተቀመጠችበት በመነሳት ልጇን አቅፋ ለማስተኛት ወደ መኝታ ክፍል ሄደች፡፡ አስተኝታ ከተመለሰች በኋላ «ቆይ ግን ተሾመ ለምን አትረዳኝም ሁላችንንም የተከበርን ሰዎች ነን፡፡ ይህ ጉዳይ ለሁለታችንም ስም ደስ አይልም፡፡ ያኔ ተሳሳትን አሁን ግን ለምን ታስጨንቀኛለህ?» እጁን በመያዝ ነበር በልምምጥ መልኩ የምታወራው፡፡

በቆመችበት ትቷት ወደ ሶፋው ሄዶ ተቀመጠና «አስጨነከኝ አልሽ? እኔስ በአንቺ የእድሜዬን እሩብ ተሰቃይቼብሽ የለም እንዴ? ዳሩ ምን ያደርጋል በመጨረሻ ተሸንፌ አጅቤ ዳርኩሽ፡፡ ተስፋ ቆርጬ ተውኩሽ፡፡ አንቺ ግን ዞረሽ መጣሽ»

«ተሾመ እኔ እኮ ባሌ ለስራ ስለሄደ አንተም እኔም የማንቀርበት ሰርግ በመሆኑም አብረን እንድንሄድ በማሰብ ነው የደወልኩልህ፡፡ አንተም ይህን ታውቃለህ» ስታስበው ዘገነናት ደግሞ ማሰብ ባትፈልገውም እሱ እየመጣ ያስጨንቃታል፡፡ «ኋላ ግን በመጠጥ ተገፋፍተን ተሳሳትን፡፡ ይህ ግን አንተ አሁን ለምትፈፅመው በደልና ለምትነሳኝ ሰላም የሚገፋፋህ አይደለም፡፡»

ቁጭ ባለበት ጀነን በማለት «ስሚ እኔ ካንቺ ምንም አልፈልግም ልጄ የእኔ መሆኑን ታውቂያለሽ ስለዚህ እንድትሰጭኝ ነው የምፈልገው፡፡ ከፈለግሽ አንቺ እዚሁ መቅረትም አልያ ደግሞ እኔን መከተል መብትሽ ነው፡፡» ሕፃኑ ተነስቶ ማልቀስ ጀምሯል የሚሰማው የለም፡፡ ኤፍሬም የሚይዘው የሚጨብጠው ጠፋው፡፡ ሊያውም መፀነሷን ካወቀ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በልጁ ብዙ ተስፋ ነበረው፡፡ አሁን የሚሰማው ነገር ተስፋው ሕልሙ እና የአይኔ ማረፊያ የሚለው ህፃን የእሱ እንዳልሆነ እየጠቆመው ነው፡፡ ተስፋም ቆረጠ እንደተሸነፈ አምኖ ቤቱን ጥሎ ሊወጣ ነበር፡፡ ሲያስበው ግን ይህ ጓደኛው መቼም እንደማይተወው አሰበ፡፡

«እባክህ ተወኝ ልለምንህ ልጄን እኔ ላሳድገው፡፡ እሱም ይህን ቢሰማ የሚፈጠረውን አስብ፡፡ እኔ የምትፈልገውን ላድርግልህ ግን ልጄንና እኔን ተወን፡፡» ብላ እግሩ ላይ ወደቀች፡፡ ይህን ሲያይ ኤፍሬም እሷ አምላኪ ጓደኛው ደግሞ ጣኦት የሆኑ መሰለው፡፡ ተሾመ ግን የእሷን መንበርከክ እንዳንጠለጠለው ከረቫት ክብር ሊሰጠው አልወደደም፡፡ ከእግሩ ላይ ገፍትሮ ጣላትና፡፡ «እስካሁንም ያዘናጋሽኝ እንዲህ እያልሽ ነው፡፡ አሁን ግን ባልሽ ሁሉን ማወቅ አለበት» አለና ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ህፃኑ ጋር ለመሄድ ተዘጋጀ፡፡

ኤፍሬም በዚህ ሰዓት በደመነፍስ ወደ ቤት ዘልቆ ገባ፡፡ ተሾመ ደነገጠ ነፃነትም እንባዋን ከአይኗ ነይ እየሞዠቀች ከተዘረጋችበት ተነሳች፡፡ ሁለቱን በጥሞና ካጤነ በኋላ ተንደርድሮ ተሾመ ላይ በመሄድ ባለው ሀይል ገፍቶት ጭንቅላቱን ከግድግዳው ጋር አጋጨው፡፡ ወዲያው ራሱን ሳተ ተሾመ፡፡ ኤፍሬም አሁንም አልተረጋጋም፡፡ ከጠረጴዛው ላይ የአበባ ማስቀመጫውን በማንሳት አናቱ ላይ ከሰከሰው፡፡ በዚህ ጊዜ ነፃነት ከድርጊቱ እንዲቆጠብ እየተማጸነችው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ አልተሳካላትም፡፡ በመሬት ውስጥ የተቀበረ የውሃ ቱቦ የፈነዳ ይመስል ከአናቱ ደሙ ይንጨረጨር ጀመር፡፡ ሕፃኑ እንጥሉ እስኪነቀል ይጮሐል፡፡ የሚሰማው የለም፡፡ ኤፍሬም ነፃነትን ሲያይ ጣረ ሞት መሰለችው፡፡ ፀጉሯን ጠምዝዞ በመያዝ እየጐተተ ወደ ጠረጴዛው አስጠጋና ከጠረጴዛው ላይ የብርቱካን መቁረጫ ቢላዋውን አንስቶ ያለ አንዳች ማቅማማት አንገቷ ላይ ሰደደው፡፡ እሷ በድንጋጤው የለመነችው ልመና እይደለም የሷን የአለም ሁሉ ሀጢያት ሊያስደመስስ የሚችል ነበር፡፡ እሱ ግን ምንም እንዳላጠፋ ሰው ወደ ህፃኑ በመሄድ የሚያዳምጠው ይመስል «አንተ በእድል ታድጋለህ» ብሎ አነሳውና እጁን ለፖሊስ ሊሰጥ በምሽት ጉዞ ጀመረ፡፡ ብቻውን እየሳቀ ጉዞ ጀመረ፡፡ በልቡ ግን ያለቅስ ነበር፡፡

# ይህ ገጽ በሊቢያ በኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ላይ በደረሰው አሰቃቂ ግድያ ሰለባ ለሆኑት መታሰቢያ ይሁንልን!!!

## ሰሙ- ሰማዕት

ዘመን አያመጣው ቀን አይጥለው የለ፣
እንደበሬ ታስሮ ወይ ሀገሬ እያለ፣
ስንቱ ያገሬ ልጅ ሕይወቱ ተለየ፡፡
ከዚህ በጉልበቱ ከዚያ በላበቱ፣
ከዚህ በትዝታ ከዚያ በናፍቆቱ፣
ተማሮ ለኖረ አንሶት ያ ልፋቱ፣
ሰይፉ ታዘዘለት አዬ ሰው ከንቱ፡፡
ኢትዮጵያ ሀገሬ ምንድነው ምስጢሩ?
ሕዝብሽ ሰው አክባሪ ለሰው ገንዘብ ኩሩ፣
ተመሳስሎ ኗሪ ባሕል ከምግባሩ፣
አልበቃው አለና ረሀብና ቁሩ፣
ከያለበት ሀገር እንዲህ መጠቆሩ፣
እኔን አልገባኝም ምንድነው ምስጢሩ?
በረሀ አቆራርጠው ጨለማውን ጥሰው፣
ረሀቡን ችለው ዋይውንም ታግሰው፣
እንደሰው ለመኖር ላባቸውን ጠርገው፣
ሲሄዱ ከሀገሩ ሰው አለ መስኳቸው፣
አይ አለመታደል ሰይፍ ጠበቃቸው፡፡
ሺህ አመት ላይኖር ሺህ ጊዜ ላይሞላ፣
የሰው ልጅ እንደ እንጨት በእሳቱ ሲበላ፣
ይበቃል ዝምታው ፈልጉለት መላ፡፡
ሰርተን ሀገርን እንለውጥ ብለው፣
ሰርተን ወገንን እንለውጥ ብለው፣
መሰላቸው እንጅ ሰርተን የምንኮራ፣
ሲሄዱ በስጋት ሲደርሱ በካራ፡፡
ከዚያ ከፎቅ ሲጣል ከዚያ በእሳት ሊቢላ፣
ሕዝባችን አለቀ አንድም ቀን ላይሞላ፡፡
በዘር መድሎ እንዲያ ሲሰቃዩ፣
አሰልጥና ስትሰድ አይተው እንዳላዩ፡፡
ዛሬ ተረሳና ያሁሉ መከራ በኢትዮጵያ እርዳታ፣
ባጕረስኩ ተነከስኩ ሆኖብን ትንታ፣
ሲቃቸውን በሳት አንገትን በካራ ሆነ ያ ውለታ፡፡
ኢትዮጵያ ሀገሬ ለፀሎት ተነሽ፣
መከራው በዛብን እንባችን አብሽ፣
ዝቅ ብሎ ይዋል ሰንደቃላማሽ፣
ክፋት የማያውቁት የግፍ ልጆችሽ፣
ከያሉበት ቦታ ተሰየፉልሽ፣
እጆችሽን ዘርጊ ወደፈጣሪሽ፣
ወንድም ወንድሙን አረደልሽ፡፡
አንጀት የለሾቹ «ISIS» የሚባሉ፣
ተነስተዋልና ሕዝብሽን ሊበሉ፡፡
ፈጥኖ ሳያጠፋን ርኩስ ግብራቸው፣
ሀገሬ እባክሽን አትቀደሚያቸው፡፡
ልባችን ታውኳል እንባችን አልቆመም፣
የልጆችሽ መቅረት ሆኖብናል ህመም፡፡
ነገ ለቀሩትስ ምን ዋስትና አላቸው?
ነፍሳቸውን አኑር ከነ አብርሃም ጋራ
ልጆችህ መጥተዋል አምላክ ሆይ አደራ፡፡
ፀሎታችን ስማ ይኖሩ ዘንድ ገነት፣
ፍጥረትህ መጥተዋል ሳይታሰብ ድንገት፡፡

ሽጋው ገብሩ

## መሰዋትነት

እህ... እህ... እራሴን አዞረኝ- ከኔ ላይ
መሰለኝ፣
ኸረ አቅለሸለሸ ጉሮሮዬን ያዘኝ፣
አይኖቼ እያዩት ቅዠትም መሰለኝ፣
አይኔን እርግብ ጭፍን መናገር አቃተኝ፣
የሰው ልጅ እንደ በግ አንገቱ ሲታረድ፣
ደማቸው እንደ ጎርፍ አሸዋ ላይ ሲወርድ፣
ቅዠትም አይደለም እውነት አየ አይኔ፣
አሸዋ ላይ ወድቆ ታረደ ወገኔ፡፡

ይህ አልበቃው ብሎ አረመኔው ገዳይ፣
ጭንቅላቱን ይዞ ጆርባው ላይ ሲያሳይ፣
የበግ እራስ ምላስ - በላች ነው መሰለኝ፣
ማንም የማይደፍረኝ ይላል እኮ ሰው ነኝ፡፡
ለዚህ የሰው አውሬ በምን ባስረዳሁት፣
አንገትን መስጠት መሆንን መስዋዕት፡፡
ስጋቸውንም አየ ደማቸውንም አየ፣
የእጁን ሰይፍ ወርውሮ ነፍሳቸውን ባየ፡፡!
እርሱ የናቃቸው በሰይፍ የቀላቸው፣
ያከበሩት አምላክ አክሊል ሲሰጣቸው፡፡

ፋንታነሽ ሳቀው
ከውስ/ግ/ኮ/ ዳይሬክተር ጽ/ቤት

---

# የናይል ጋዜጣ አዘጋጆች በኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ላይ በሊቢያ በደረሰው አሰቃቂ ግድያ የተሰማንን ጥልቅ ሀዘን እየገለጽን ለቤተሰቦቻቸውና ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መጽናናትን እንመኛለን፡፡ ክብር ለወገኖቻችን!!!

## “ይህን ትልቅ መስዋእትነት እየከፈለ ያለው የአካባቢው ሕብረተሰብ ነው፡፡”

ከገጽ 9 የዞረ

የለውም፡፡ ከዛ ባሻገር የሐይቁን ዳርቻ ሙሉ በሙሉ ስለሚሸፍነው በውስጡ የሚገኘው ማንኛውም ሕይወት ያለው ነገር ያጠፋል፡፡ ማንኛውንም እንስሳትና ተክሎችን ማጥፋት ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት አካባቢውን ይወረዋል፡፡ ስለዚህ በባዮዳይቨርሲቲውና በውሃው ስነ ምህዳር ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ከኢኮኖሚ አንጻርም ችግር እየፈጠረ ነው፡፡ የሐይቁ ዳርቻ ለአካባቢው ሕብረተሰብ ለግጦሽ የሚያገለግል ቢሆንም ከብቶቻቸውን እንኳን ወደ ሐይቁ አስገብተው ለማጠጣት ችግር ይገጥማቸዋል፡፡ በርግጥ አሁን ላይ የፒኤችዲና የማስተር ተማሪዎች በዚህ ዙርያ ጥናት እያደረጉ ነው፡፡ በዚህም በቅርብ ቀን ውጤት ይገኛል ብለን እንጠብቃለን፡፡

ናይል፡- በእንቦጭ አረም ዙርያ በተለያዩ መድረኮች ለሚመለከታቸው አካላት አቅርበዋል፡፡ ምላሹ ምን ነበር?

ዶ/ር ዋሴ፡- እንግዲህ እንደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ያደረግነው ይህን ጥናት ካጠናን በኋላ ለሚመለከተው አካል ጉዳዩን ማሳየትና ማስረዳት ነው፡፡ እኛን የሚመለከተንም ይኸው ነው፡፡ ያደረግነው መጀመሪያ የክልሉ መንግስትን ማሳመን ነው፡፡ በዚህም የክልሉ መንግስት ሙሉ በሙሉ ጉዳዬ ነው ብሎ ይዞታል፡፡ ትልቁ ነገር ይህ ነው፡፡ ይህ ነገር ትንሽ በጀት (resource) የሚፈልግ ጉዳይ ስለሆነ የአለም አቀፉ ሕብረተሰብም በተለይም ለጋሽ ድርጅቶች (donors) የምንላቸው እንዲያግዙን ወርክ ሾፕ አዘጋጅተን ነበር፡፡ ታሕሳስ ወር መጀመሪያ አካባቢ ብዙ አዲስ አበባ የሚገኙ ብሄራዊና አለም አቀፋዊ ድርጅቶችን ጠርተን ውጤታማ የሆነ ወርክ ሾፕ አካሂደናል፡፡ ከዚህ ወርክ ሾፕ ካገኘናቸው ውጤቶች መካከል እንግዲህ አንዳንዶቹ ድርጅቶች አንዳንድ ስራዎችን ለማስተባበርና ለማቀናጀት ለአካባቢ ጥበቃ ቢሮ እየሰጡ ነው፡፡ አሁንም እንጠብቃለን፡፡ በተለያዩ መድረኮች በተገኘው አጋጣሚ ይሄንን አደገኛ መጤ ተስፋፊ አረም ጣና ውስጥ በቁጥጥር ውስጥ ለማዋል የተቻለንን ሁሉ እያደረግን ነው፡፡ እኔ ብቻ ሳልሆን ዩኒቨርሲቲውና በዚህ ቲም የተዋቀረው ሁሉ ስለአረሙ አሳሳቢነት ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያቀርባል፡፡ ሃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል፡፡

ናይል፡- በአካባቢው ላይ ካለው ማሕበረሰብ ምን ይጠበቃል?

ዶ/ር ዋሴ፡- እውነቱን ለመናገር የአካባቢው ማህበረሰብ በጣም በጣም በትግል ላይ ነው ያለው፡፡ ሄደው በጉልበት ውሃ ውስጥ ገብተው አረሙን ሲያወጡ መዋል በጣም ፈታኝ ነው፡፡ በጣም ከባዱ ሥራ ነው፡፡ እስካሁን በቴክኖሎጂ አላገዝናቸውም፣ በምርምር አላገዝናቸውም፡፡ ለወደፊቱ በዚህ ጉዳይ ነው ዩኒቨርሲቲው ለመስራት እያቀደ ያለው፡፡ ሕብረተሰቡን በቴክኖሎጂ ማገዝ ለምሳሌ የሚያወጡበት ጀልባ፣ የሚያወጣበት መሳሪያ (በዘመናዊ መንገድ አጭዶ የሚያወጣ መሳሪያ) ወይም ደግሞ በስነሕይወታዊ ዘይቤ ለምሳሌ ጢንዚዛ አራብተን የምንለቅበት ሁኔታ ቢፈጠር አረሙን ብቻ የሚበላ ጥንዚዛ ስላለ በመልቀቅ ሕብረተሰብን መታደግ ነው ያለብን ብለን ነው የወደፊት አቅጣጫ የያዝነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ግን ተወደደም ተጠላም ይህን ትልቅ መስዋእትነት እየከፈለ ያለው የአካባቢው ሕብረተሰብ ነው፡፡ የአካባቢው ሕብረተሰብ ሙሉ በሙሉ ውሃው ውስጥ በመግባት አረሙን ለማጥፋት እየታገለ ነው ያለው፡፡ ሁሉም ሰው ሄዶ ቢያየው ወይም በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ቢከታተል የአካባቢው ሕብረተሰብ ምን ያህል እየተረባረበና እየታገለ እንደሚገኝ መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንደዚህ አይነት ስራ በጣም ፈታኝ ነው፡፡ የተለያዩ ችግሮች ለምሳሌ አለቅት አለ፤ በእባብ መነደፍ አለ፡፡ እነዚህን እክሎች በመቋቋም ሕብረተሰቡ እየታገለ ነው፡፡ እንዲያውም እኛ በሚገባው መንገድ እያገዝነው አይደለም፡፡

ናይል፡- ለሌሎች ተመራማሪዎችና ምሁራን ማስተላለፍ የሚፈልጉት ካለ?

ዶ/ር ዋሴ፡- ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እውነቱን ለመናገር ለማሕበረሰቡ ሰፊ አገልግሎት በመስጠት ላይ ነው፡፡ አሁንም እየሰራ ያለው ጣናን መታደግና መንከባከብ ነው፡፡ ቅድሚያ እየሰጠነው ያለው የመጀመሪያ ቦታችን ጣና ላይ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ጣና ላይ ትኩረት የሚሰጥ ከሆነ ጣና ላይ ብዙ ምርመሮች እንዲሰሩ ይፈለጋል፡፡ ለምሳሌ አሁን እየተሰራበት ያለውን የደንገል ፕሮጀክት ጣና ላይ እየተከልነው ነው፡፡ እሱን ማስፋፋት እንፈልጋለን፡፡ ምክንያቱም ይሄን እንቦጭ (water hyacinth) ለመቋቋም አንዱ መንገድ ደንገሉን ማስፋፋት ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ስራዎች ላይ መምህራንም ሌሎች ሰራተኞችም አቅማቸው በፈቀደ መጠን ምርምርም ሆነ ሌሎች ማንኛውንም የአካባቢ ጥበቃ ስራ ቢሰሩ በተለይ እኛ እየመራነው ያለውን የምርምር ቲም በጸጋ ነው የምንቀበላቸው ወይም እንዲበረታቱ የምንፈልገው፡፡ መምህራንም የአስተዳደር ሰራተኛውም ለጣና አምባሳደሮች ቢሆን ደስ ይለኛል፡፡ ሁሉም በርግጥ ለጣና የተቆርቋሪነት ስሜት ስላለው ትኩረት እንደሚሰጥ አውቃለሁ፡፡ ጣና አንድ ትልቁ ሐብታችን ነው፡፡ እንዲውም አንድ ትልቅ ባለስልጣን ሲናገሩ አባይ ግድብን ገድበን ልናቆመው እንችላለን፡፡ ሰው ሰራሽ ነው፡፡ ጣናን ግን ተመልሰን ልንሰራው አንችልም፡፡ ስለዚህ መጠበቅ አለብን፡፡ ከዛም በላይ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ሐይቅ ነው፡፡ በተለይ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በሐይቁ አናት ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የሚገባውን መወጣት አለበት፡፡ እንደ ግለሰብም እንደ ዩኒቨርሲቲም፡፡

ናይል፡- ስለነበረን ቆይታ ከልብ እናመሰግናለን!!

ዶ/ር ዋሴ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹሁፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በኢሜል አድራሻችን በመላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# የዶ/ር ቴዎድሮስ በካፋ ዜና እረፍትና አጭር የሕይወት ታሪክ

በታድዬ አስማረ



በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ መምህርና የኢኮኖሚክ ምርምር ዳይሬክተር የነበሩት ዶ/ር ቴዎድሮስ በካፋ ሚያዚያ 03/2007 ዓ.ም በድንገተኛ ህመም ምክንያት አርፈዋል፡፡ ዶ/ር ቴዎድሮስ በተወለዱ 55 ዓመታቸው ከዚህ አለም የተለዩ ሲሆን የቀብር ስነስርዓታቸው ሚያዚያ 04 ቀን 2007 ዓ.ም በባሕር ዳር ፈለገ ቅዱስ ሚካኤል አንድነት ገዳም ተፈፅሟል፡፡

ዶ/ር ቴዎድሮስ በካፋ ከአባታቸው ከአቶ በካፋ የኔነህ ከእናታቸው ከወ/ሮ የሩቅነሽ ምትኩ በድሮ አጠራሩ በጐጃም ክ/ሀገር ደብረማርቆስ ከተማ በ1952 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ በቤተሰቦቻቸው እንክብካቤ ካደጉ በኂላ አቅማቸው ለትምህርት እንደደረሰ የ1ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዳንግላና በብቸና ከተሞች ተዘዋውረው የተከታተሉ ሲሆን የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በደብረማርቆስ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተከታትለው አጠናቀዋል፡፡ የ12ኛ ማጠቃለያ ፈተና ወስደው የዩኒቨርሲቲ የመግቢያ ጥሩ ውጤት በማምጣታቸው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግራያቸውን ይዘዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመርቀው እንደወጡ ከ1977-1979 ዓ.ም በምስራቅ ኢትዮጵያ ፕላን ቀጠና ጽ/ቤት የንግድና ኢንዱስትሪ መምሪያ ኃላፊ ሰርተዋል፡፡ በመቀጠል የማስተርስ ዲግሪያቸውን ለመማር ወደ ኔዘርላንድ የሄዱት ዶ/ር ቴዎድሮስ በ1981 ዓ.ም ወደ ሀገራቸው በመመለስ ለሁለት ዓመት ማለትም ከ1981-1982 ዓ.ም የምስራቅ ጐጃም ዞን የኢኮኖሚክስ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል፡፡

ዶ/ር ቴዎድሮስ ሀቢታት በተባለ ድርጅት ውስጥ በመግባት በከፍተኛ የኢኮኖሚክስ ባለሙያነት (ኢኮኖሚስትነት) ከ1982-1985 ዓ.ም ሲያገለግሉ ከቆዩ በኂላ ወደ አብክመ በመዛወር የክልሉ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን አገልግሎለዋል፡፡ ከ1988-1991 ዓ.ም ደግሞ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ ሆነው እያገለገሉ እያለ የትምህርት እድል በማግኘታቸው እንደገና ወደ ኔዘርላንድ ሄግ በመሄዱ የዶክትሬት ድግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡ ከኔዘርላንድ በመመለስም የክልሉ ፕሬዚዳንት ከፍተኛ የኢኮኖሚ አማካሪ ሆነው አገልግለዋል፡፡

መንግስት በሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎችን ሲያስፋፋ ዶ/ር ቴዎድሮስ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ መስራችና ፕሬዚዳንት በመሆን ከ1998-2005 ዓ.ም በዩኒቨርሲቲው በርካታ ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡

በመጨረሻም ዶ/ር ቴዎድሮስ ወደ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመዛወር በዩኒቨርሲቲው የኢኮኖሚ ምርምር ተቋም ዳይሬክተር በመሆን እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ በአጠቃላይ ዶ/ር ቴዎድሮስ በካፋ ለሀገራቸው እንዲሰሩ በተመደቡበት የስራ ኃላፊነት እና ሙያ በታታሪነትና በቅንነት ያገለገሉ ምሁር ናቸው፡፡ ከሙያና ከስራ ኃላፊነት በተጨማሪ ከ15 በላይ ሙያዊ የምርምር ውጤቶችን ሰርተው አበርክተዋል፡፡

ዶ/ር ቴዎድሮስ በባሕሪያቸው ቅን፣ ተግባቢ፣ ተጫዋች እና ለሰው አዛኝና ሰውን መርዳት የሚወዱ ሀገር ወዳድ ሰው ነበሩ፡፡ ዶ/ር ቴዎድሮስ ባለትዳርና የአራት ልጆች አባትም ነበሩ፡፡

## የናይል ጋዜጣ አዘጋጆች እንዲሁም የውስጥ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ለቤተሰቦቻቸውና ወዳጅ ዘመዶቻቸው መፅናናትን ይመኛል፡፡




መስ ኮ ተ ጥበ ብ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴሌቪዥን ፕሮግራም

በአማራ ቴሌቪዥን በመደበኛ ስርጭትና በናይል ሳት በኢትዮጵያና በመላዉ ዓለም ለሚገኙ ተመልካቾች መተላለፍ ይጀምራል፡፡

በቅርብ ቀን ይጠብቁን!

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ